GEBECON PLC

# ገምሹ በየነ ኮንስትራክሽን
ኃ/የተ/የግል ኩባንያ

# GEMSHU BEYENE CONSTRUCTION PLC

*Paving the Road for Development !!*



ዓመታዊ መጽሔት፤ ነሐሴ 2008
Annual Publication, August 2015

GEBECON PLC

ገምሹ በየነ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ኩባንያ

**GEMSHU BEYENE CONSTRUCTION PLC**

Tel. 0116189550
Fax 0116630462
PO Box: 29228
Addis Ababa, Ethiopia
Email: info@gebeconstruction.com
www. gebeconstruction.com

***Paving the Road for Development !!***

# ማውጫ
# Contents


| | | |
|---|---|---|
| 1 | **የዋና ሥራ አስኪያጁ መልዕክት**<br>**Message from the General Manager** | 8 |
| 2 | **የምክትል ዋና ሥራ አስኪያጁ መልዕክት**<br>**Message from the Deputy General Manager** | 10 |
| 3 | **ከልዩ እንግዳችን ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ**<br>**Interview with Our Special Guest** | 12 |
| 4 | **የገበኮን ዕድገት ምልከታ**<br>**Tracking the Growth of the Company** | 18 |
| 5 | **ዓመታዊ የኩባንያው የፕሮጀክቶች የሥራ አፈጻጸም**<br>**Company Annual Project Performance** | 20 |
| 5.1 | የዲማ- ፍየል ውሃ የአስፋልት መንገድ ሥራ ፕሮጀክት<br>Dima-Fiyel Wuha Asphalt Road Project | 23 |
| 5.2 | የአዘዞ ጎርጎራ የአስፋልት የመንገድ ሥራፕሮጀክት<br>Azezo-Gorgora Upgrading Asphalt Road Project | 23 |
| 5.3 | የመሃል ሜዳ - ዓለም ከተማ የአስፋልት መንገድ ሥራ ፕሮጀክት<br>Mehalmeda-Alemketema Road Project | 25 |
| 5.4 | የሐረር ተለዋጭ አስፋልት መንገድ ፕሮጀክት<br>Harar-By -Pass Asphalt Road Project | 26 |
| 5.5 | የአምቦ ከተማ የውስጥ ለውስጥ አስፋልት መንገድ ፕሮጀክት<br>Ambo Town Internal Asphalt Road Project | 28 |
| 5.6 | የኢሊሊ ኢንተርናሽናል ሆቴል ሁለገብ ህንጻ ግንባታ ፕሮጀክት<br>Elilly Multipurpose Building Complex Project | 30 |
| 5.7 | የአርሲ ዩኒቨርሲቲ ህንጻ ግንባታ ፕሮጀክት<br>Arsi University Building Project | 31 |
| 6 | **ዓመታዊ የጠቅላላ ሠራተኞች ስብሰባ**<br>**Annual Staff Assembly Meeting** | 32 |
| 7 | **የገበኮን ፕሮጀክቶች ዕቅድና አፈጻጸም ግምገማ**<br>**Project Plan Performance Review Meeting** | 34 |
| 8 | **የገበኮን አምስት ዓመት ስትራቴጂ ዕቅድ ዝግጅት ምዘና ወርክሾፕ**<br>**Five Years Strategic Plan Development Revalidation Workshop** | 35 |
| 9 | **የሰው ኃይል ልማትና ሥልጠና ሥራዎች እንቅስቃሴ**<br>**Staff Training and Development Activities** | 36 |
| 10 | **የኮንስትራክሽን ፕላኒንግ እና ኮንትራት አስተዳደር እንቅስቃሴዎች**<br>**Construction Planning and Contract Administration Activities** | 38 |
| 11 | **ወደፊት አርቆ መመልከት - የስትራቴጂ ዕቅድ ዝግጅት**<br>**Looking Ahead - Strategic Plan Development** | 40 |
| 12 | **ከሐረር ተለዋጭ አስፋልት መንገድ ፕሮጀክት የተወሰዱ ተሞክሮዎች**<br>**Lessons From Harar-By-Pass Asphalt Road Project** | 45 |
| 13 | **ኢሊሊ ኢንተርናሽናል ሆቴል ፡ በላቀ አፍሪካዊ መስተንግዶ**<br>**Elilly International Hotel: Redefining African Hospitality** | 49 |

# የገበኮን፡ ራዕይ ፣ ተልዕኮና እሴቶች

## ራዕይ

የገበኮን ራዕይ በኮንስትራክሽን ዘርፍ በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና ያለውና ግንባር ቀደም ኩባንያ ሆኖ መገኘት ነው።

## ተልዕኮ

ተልዕኮአችን ከፍተኛ የጥራት ደረጃ ያላቸው የግንባታ ሥራዎችን በተመጣጣኝ ወጪና በኮንትራት ውል መሠረት በወቅቱ አጠናቅቆ በማስረከብ ደንበኞቻችንና ባለድርሻ አካላትን ማርካት ነው።

ይህንን ተልዕኮአችንን ለማሳካት የምንከተላቸው ስልቶች፤

- ዘመናዊ የኮንስትራክሽን ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀምና ጠንካራ የማኔጅመንት ሥርዓት በመዘርጋት የኩባንያው የፋይናንስ አቅም አስተማማኝ ማድረግ፤
- አዳዲስ ለውጦችን ከተወዳዳሪዎቹ ቀድሞ በጥራትና ቅልጥፍና ተግባራዊ በማድረግ በአገሪቷ የኮንስትራክሽን ማኔጀመንት ጥራት ማሳደግ፤
- የኩባንያውን የውስጥ አቅም ለመገንባትና የተሻሻሉ የኮንስትራክሽን ማኔጀመንት ዘዴዎችን ለመጠቀም በአገር ውስጥና በዓለም አቀፍ ደረጃ ታዋቂ ከሆኑ የውጭ አገር የኢንጂነሪንግ ዲዛይንና ኮንስትራክሽን ኩባንያዎች ጋር ተባብሮ መሥራት፤
- የግንባታ ሥራዎችን በተፈለገው ጥራትና ጊዜ እንዲጠናቀቁ አስተማማኝ አቅርቦት መኖሩን ለማረጋገጥ በግንባታ ማቴሪያሎች አቅርቦት ሥራ ውስጥ መግባት።

## እሴቶች

- የተሻለ የሠራተኛ ተነሳሽነትና ቆይታን ማበረታታት፤
- የቡድን ስሜትና ምን ጊዜም የመማር ዝንባሌን ማሳደግ፤
- መልካም ባህሪያትን (ሐቀኝነት፤ታማኝነትና የዳበሩ እውቀቶችን) ማበረታታትና በሞዴልነት መጠቀም፤
- ለሠራተኞቻችን ትኩረት ሰተን የእነሱን ሙሉ ድጋፍና ቁርጠኛ ተሳትፎ ማሳደግ፤
- ከባለድርሻ አካላት ጋር ቀጣይነት ያለው ግንኙነት ማዳበር፤
- ለውጦችን በመልካም አጋጣሚነት መውሰድ፤
- ግልጸኝነት፤ተጠያቂነትና የሙያ ሥነ-ምግባር በኮንስትራክሽን ዘርፍ ማስፋፋት።

# VISION, MISSION AND VALUES OF GEBECON PLC

## VISION

GEBECON PLC envisions becoming an internationally reputable and leading company in the construction sector.

## MISSION

Our mission is to meet the expectations of our clients and stakeholders by constructing high quality construction works at reasonable cost and within the contract period.

To achieve our mission, we:

Put in place strong and modern construction management systems and technologies to grow into a financially sound construction company;

- Take a long term perspective by implementing important changes, more effectively and efficiently than our competitors, to improve the quality of road construction management in the country;
- Partner with renowned and important companies engaged in the area of engineering design and construction, local and overseas, as a strategy to build in-house capacity and facilitate the adoption of best construction management practices; and
- Engage in the business of construction related supplies to ensure reliability and delivery of construction works on time and within stated quality standards.

## VALUES

- Foster improved staff motivation & retention.
- Cultivate life-long learning and employee team spirit.
- Model and reward good behavior (honesty, loyalty, resourcefulness.)
- Treasure staff to gain their full support and commitment.
- Build & maintain synergy with stakeholders.
- Embrace challenge as an opportunity, and
- Promote transparency, responsibility and professionalism in the construction sector

# ከፍተኛ የሥራ አመራር አባላት
# TOP MANAGEMENT MEMBERS



**Gemshu Beyene**
General Manager



**Girma Guluma**
Deputy General Manager



**Asfaw Diribssa**
Manager, Construction Planning and Contract Administration Dep't



**Fekadu Abera**
Director, Construction Works Dep't



**Kelbessa Eticha**
Manager, Finance and Accounts Dep't



**Samuel Seife**
Manager, Building Construction and Real Estate Dev't Dep't



**Emana Merga**
Manager, Plant & Equipment- Dep't



**Mamo Afeta**
A/Manager, HR and Administration Dep't



**Daniel Kebebe**
A/Manager, Procurement and Property Adm. Dep't



**Jiregna Lemessa**
Head, Legal Services



**Girma Gudissa**
Head, Planning and Business Dev't



**T/Michael Zewude**
Head, Audit Services

## የፕሮጀክት ኃላፊዎች
## PROJECT MANAGERS



**Abera Merga**
Project Manager, Azezo Gorgora Road Project



**Henock Mebrate**
Project Manager, Harar-By-Pass Road Project



**Worku Kuma**
Project Manager, KM72-Alemketema Road Project



**Alemayehu Denboba**
Project Manager, Elilly Multipurpose Building Complex Project



**Fekede Waquma**
Project Manager, Arsi University Building Project



**Oliyad Tefera**
A/Project Manager, Ambo Town Internal Asphalt Road Project

# 1 የዋና ሥራ አስኪያጁ መልዕክት
# MESSAGE FROM THE GENERAL MANAGER



**አቶ ገምሹ በየነ**
ዋና ሥራ አስኪያጅ
**Ato Gemshu Beyene,**
General Manager

እንዳለፉት ዓመታት ሁሉ 2008 ዓ.ም ኩባንያችን እጅግ የላቀ ውጤት ያስመዘገበበት ዓመት ነው፡፡ ምንም እንኳን በርከት ያሉ ውስጣዊና ውጫዊ ተግዳሮቶች ቢያጋጥሙንም ለኩባንያች ዓመታዊ ዕቅድ መሳካት ያሳየነው ያላሰለሰ ቁርጠኝነት በከፍተኛ ሁኔታ የሚደነቅ ነው፡፡

የፕሮጀክቶቻችን (ማለትም በህንጻና በመንገድ ዘርፍ) አፈጻጸም ለማሳካትና ከደንበኞቻችን ጋር የገባነውን የኮንትራት ግዴታ በተገቢው መልኩ ለማሟላት ሁሉን አቀፍ ጥረት አድርገናል፡ ፡ በዚህም ረገድ የታዩት መሻሻሎችና ውጤቶች እጅግ አበረታች ናቸው፡፡ በፋይናንስ ውጤት ረገድም በ2008 በጀት ዓመት የሒሳብ መዝጊያ በጠቅላላው ኦዲት ያልተደረገ ገቢ (unaudited annual turnover) ከ650 ሚሊዮን ብር በላይ ተመዝግቧል፡፡

በዕቅድ የተከናወነው የዓመቱ የኩባንያው የመንገድ ፕሮጀክቶች የሥራ እንቅስቃሴ እጅግ አበረታች ነበር፡፡ ከጥቃቅን ሥራዎች በስተቀር የሐረር 20 ኪሜ ተለዋጭ አስፋልት መንገድ ፕሮጀክትን ኩባንያው አጠናቋል፡፡ እስከ ሰኔ 2008 ዓ.ም የአዘዞ-ጎርጎራ አስፋልት መንገድ ፕሮጀክትንም እንዲሁ ከ90 ፐርሰንት በላይ ማጠናቀቅ ተችሏል። ምንም እንኳን በርከት ያሉ ውጫዊ ተግዳሮቶች ቢያጋጥሙም የመሃል ሜዳ-ዓለም ከተማ አስፋልት መንገድ ሥራ ፕሮጀክትም አመርቂ ሒደት አሳይቷል፡፡ ሌላው የዓመቱ ዋነኛ ስኬት ሆኖ የተመዘገበው የኢሊሊ ኢንተርናሽናል ሆቴል አካል የሆነው ባለ 22 ፎቅ ዘርፈ ብዙ ህንጻ መዋቅር እና ዋና ዋና የግንባታ ክፍሎች መጠናቀቅ ነው፡፡

በዚሁ ዓመት ኩባንያችን 508 ሚሊዮን ብር በሚጠጋ የገንዘብ መጠን የአምቦ ከተማን የውስጥ ለውስጥ አስፋልት መንገድ ለመገንባት አዲስ የኮንትራት ስምምነት ከኦሮሚያ መንገዶች ባለስልጣን ጋር በየካቲት ወር 2008 ዓ.ም የተፈራረመ ሲሆን ፤ ይህም ኩባንያው በኦሮሚያ ክልል አሻራውን እንዲያሳርፍ አስችሎታል፡፡ በአራት ዓመታት ውስጥ እንደሚጠናቀቅ የሚጠበቀው የአምቦ ከተማ መንገድ ፕሮጀክት 15 ኪሜ የሚረዝም ሲሆን በአማካይ ከ18 እስከ 30.5 ሜትር ስፋት ይኖረዋል፡፡ ከነዚህም ሌላ ከአርሲ ዩኒቨርሲቲ ጋር 361 ሚሊዮን ብር በሚጠጋ የገንዘብ መጠን የተፈረመው የህንጻ ግንባታ ኮንትራት የዓመቱ ጉልህ የሥራ ስምምነት ነው፡፡

መጪው 2009 ዓ.ም የሥራ ዘመን ኩባንያችን ሁለተኛውን የአምስት ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ መተግበር የሚጀምርበት ዓመት ነው፡፡ በግንባታው ኢንደስትሪ ዘርፍ የገበያ ድርሻችንን በማሳደግና በዕቅድ ከያዝነው የዕድገት እና ስትራቴጂ አንፃር በመስራት የኩባንያችንን ደረጃ በማጠናከር ተፎካካሪነቱን ላቅ ባለ መልኩ እናስቀጥላለን። በዚህም መሠረታዊ ሥራዎቻችንን በማሰባጠር ፣ በቴክኖሎጂ እና በሰው ኃብት ልማት ላይ ትኩረት እናደርጋለን፡፡ ከሀገራችን ሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ተግባራዊነት ጎን ለጎን የስትራቴጂ ግቦች እና ዓላማዎቻችን እንደሚሳኩ ሙሉ እምነት አለኝ፡፡

ለኩባንያችን ካስቀመጥናቸው ግብና ራዕይ ጋር በስኬት ወደ ፊት እንድንጓዝ አቅም ለሆኑን እንዲሁም ድጋፍ ላደረጉልን ደንበኞቻችን ፣ ለሥራ አጋሮቻችን እንዲሁም ለመንግሥት ተቋማት ልባዊ ምስጋናዬን በዚህ ልዩ አጋጣሚ ለመግለፅ እወዳለሁ፡፡ ለኩባንያው የላቀ የሥራ አፈጻጸም ሳይታክቱ ዘወትር እየሠሩ ላሉ የኩባንያችን የሥራ አመራር አባላት እና ሰራተኞች ላቅ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

አዲሱ ዓመት የደስታና የብፅግና እንዲሆንልን እመኛለሁ፡፡

አመሰግናለሁ!

Like the preceding years, the year 2015/16 saw our company another extraordinary achievement. The commitment we have shown in meeting our company's annual targets during the reporting period is remarkably high and praiseworthy, despite the many internal and external challenges.

We have made a concerted effort in ensuring the progress of our projects (both road and building) in view of fulfilling our contractual obligations with our clients. Both the progresses and achievements made in this regard are quite encouraging. Financially, we have managed to achieve a consolidated but unaudited annual turnover of over Birr 650 million at the end of the reporting period.

The road project work progress of the company during the year was very impressive and the execution was in line with our plan. The company completed Harar-By-Pass Asphlat Road Project (20KM) with the exception of minor ancillary works. The company also substantially completed over 90 percent of Azezo Gorgora Asphalt Road Project up to the end of June 2016. The progress of Mehalmeda – Alemketema Asphalt Road Project was also commendable despite enormous external challenges. The other major achievement during the reporting period was the completion of the construction of the structure and major block works of Elilly International Hotel's 22 multipurpose story building complex project.

During the reporting period, our company entered into a new contract agreement for the construction of Ambo Town Internal Asphalt Roads Project, which worth close to Birr 508 million. The agreement, which landed the company's footprint in the Oromia Region, was signed with the Oromia Roads Authority (ORA) in February 2016. The Road project stretches over 15KM with an average span of ranging from 18m to 30.5m and expected to be completed within four years time. Another notable success during the fiscal year was the signing of a contract agreement with Arsi Univerisy for the construction of building valued at close to Birr 361 million.

As we look forward to 2016/17, our company will start implementing its second five year strategic plan. We continue to create a competitive edge in the construction industry, increase our market share, and strengthen the position of our company in line with our growth strategy. To this end, we focus our efforts in diversifying our core business activities and will continue investing in technology and human resources development in the years to come. We have no doubt that our strategic goals and objectives will come true along with the realization of our country's second GTP.

Let me seize this great opportunity to express my sincere appreciation to our clients, business partners, and government institutions who have given us the energy and enthusiasm to move forward with the ambition and vision we set for our company. My special appreciation also goes to the management team and employees of the company who have always been relentlessly working to excite superior company performance.

I wish you a happy and prosperous Ethiopian New Year!!

Thank You!!

# 2 የምክትል ዋና ሥራ አስኪያጁ መልዕክት
# MESSAGE FROM THE DEPUTY GENERAL MANAGER



**ኢንጂነር ግርማ ጉሉማ**
ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጅ
**Eng. Girma Guluma,**
Deputy General Manager

በገበኮን ኩባንያ ፋይዳችን በዋነኝነት የሚለካው ለክቡራን ደንበኞቻችን በምናቀርበው ውጤት መጠን ብቻ እንደሆነ እንገነዘባለን፡፡

ባለፉት አምስት የዕድገት አመታት ገበኮን ያጋጠሙትን የተለያዩ ተግዳሮቶች በስኬታማነት ማለፍ መቻሉ በኢትዮጵያ እንደ አንድ የግንባታ ኩባንያ በተለይም በመንገድ ግንባታ ዘርፍ ልቆ የወጣበትን ምዕራፍ እንዲጽፍ አስችሎታል፡፡

በአሁኑ ወቅት ኩባንያው የተሰማራባቸውን የግንባታ ሥራዎች በማስፋፋት ወደ ሕንፃ ግንባታ ሥራዎችም በሰፊው እየገባ ይገኛል፡ ፡ ለዚህም ማሳያ በአመርቂ ሒደት ላይ ከሚገኘው ከኢሊሊ ኢንተርናሽናል ሆቴል የመኪና ማቆሚያ እና ዘርፈ ብዙ የህንፃ ግልጋሎት ፕሮጀክት ባሻገር ከአርሲ ዩኒቨርሲቲ ጋር 361 ሚሊዮን ብር በሚጠጋ ወጪ የዩኑቨርሲቲውን ህንፃ ግንባታ ኮንትራት ውል ስምምነት ለመፈራረም ችሏል፡፡

በተጠናቀቀው የበጀት ዓመት ኩባንያው የሐረር ተለዋጭ አስፋልት ኮንክሪት መንገድ ፕሮጀክትን እና የአዘዞ-ጎርጎራ /Double Bitumen surface Treatment/ መንገድ ፕሮጀክትን አጠናቆ ለማስረከብ አቅዶ ነበር፡፡

በዚሁ መሰረት የሐረር ተለዋጭ /Harar By-Pass/ መንገድ ፕሮጀክት የተጠናቀቀ ሲሆን፤ የአዘዞ -ጎርጎራ ፕሮጀክት ግን በተያዘለት ጊዜ መጠናቀቅ አልቻለም፤ ለዚህም ዋናው ምክንያት ከኮንትራክተሩ አቅም በላይ የሆኑ የወሰን ማስከበርና የመሣሰሉት ችግሮች /Obstructions/ ናቸው፡፡ ይሁንና ይህ ፕሮጀክት በአሁኑ ወቅት 90% የሚሆነውን የፕሮጀክት ሥራ የፈፀመ ሲሆን ቀሪው 10% የሚሆነው የፔቭመንት ሥራ (Base Course & Asphalt) የማልበስ ስራ በመጪዎቹ ጥቂት ወራት ውስጥ ተሰርቶ ይጠናቀቃል፡፡ በተያያዘም የመሐል-ሜዳ አለም ከተማ መንገድ ፕሮጀክትም አብዛኛውን የአፈር ሥራ ያከናወነ ሲሆን የፕሮጀክቱ አፈፃፀምም 51% ላይ ደርሷል፡፡

ከነዚህ ፕሮጀክቶች በተጨማሪ ገበኮን ከኦሮሚያ መንገዶች ባለሥልጣን ጋር 508 ሚሊዮን ብር በሚጠጋ ወጪ የአምቦ ከተማን የውሰጥ ለውስጥ አስፋልት ኮንክሪት መንገድ ለመገንባት ስምምነት ተፈራርሟል፡፡ ይህንንም ተከትሎ የቢሮና የመኖሪያ ካምፕ ግንባታ፣ ለመንገዱ ግንባታ የሚያስፈልጉ ግብአት መገኛ ቦታዎችን መለየት፣ የቅየሳ ሥራ፣ ክረሸር ተክሎ ጠጠር የመፍጨት ስራ፣ የመንገዱን ወሰን ለማስከበር የሚያስፈልጉ መረጃዎች ማዘጋጀት /Obstruction listing/ እና የዲዛይን ሥራዎች እየተሰሩ ይገኛል፡፡

በመጪው የበጀት ዓመት ኩባንያው ከዚህ በታች የተመለከቱትን ሥራዎች ለማከናወን አቅዷል፡፡

- የአዘዞ -ጎርጎራ መንገድ ፕሮጀክትን ማጠናቀቅ፣
- የኩባንያውን የዕቃ ግዢና ንብረት አስተዳደርና የመሣሪያዎችና ፕላንት አስተዳደር ማጠናከር፣
- የዓለም ከተማ መንገድ ፕሮጀክትን ቢያንስ 85% ያህል ማጠናቀቅ፣
- በሁሉም የመንገድና የህንፃ ግንባታ ፕሮጀክቶች ላይ የላቀ አፈፃፀም ማሳየት እና፣
- የኩባንያውን የውስጥ አሠራር በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ማጠናከር ነው፡፡

በመጨረሻም ለመላው ሠራተኞቻችን ለኩባንያው ስኬት ላበረከቱት አስተዋአፆ እንዲሁም ላሳዩት ትጋት ጥልቅ ምስጋናና አክብሮታችንን እንገልፃለን፡፡

አዲሱ ዓመት የደስታና የብልፅግና ይሁንላችሁ!!

At GEBECON, we know that the only real measure of our worth is in the result we deliver to our esteemed customers.

Over the past five years of development, GEBECON PLC has managed to overcome various challenges in order to write its chapter as a renowned construction company in Ethiopia, especially in the field of road construction works.

These days, the company is diversifying its construction works to include building construction as a result of which it recently signed a contract agreement with Arsi University at a cost of close to ETB 361 million in addition to Elilly International Hotel Parking and Multiuse building complex Project, which is on good progress.

The company planned to complete and deliver Harar-By-Pass Asphalt Concrete Road Project and Azezo - Gorgora DBST Road Project in this fiscal year.

Accordingly, Harar by Pass Project is substantially completed whereas Azezo-Gorgora project is not due owing to the problem related to the timely removal of obstructions within the road corridor on time. However, the project has done considerable works, that is, about 90% of the work is finalized and left with 10%, which mainly includes base course and asphalt activities that will be concluded in the coming few months. Likewise, the whole excavation works except rock of km 72- Alemketema Road Project is roughly finished and about 51% of the project works is completed.

Moreover, GEBECON PLC has signed a contract agreement with the Oromia Roads authority for the construction of Ambo Town Asphalt Concrete Road Project at a cost of close to ETB 508 million Consequently, activities such as: - camp construction, identification of construction material sites, crushing, surveying, obstruction listing, design and so forth are on progress.

In the coming budget year, the company has planned the following activities:-

- Completion of Azezo-Gorgora Project.
- Strengthening the equipment administration and maintenance department.
- Strengthening the establishment of IT supported systems.
- Achieving sizeable work at least 85% of km 72-Alemketema Road Project, and
- Attaining remarkable achievement on all other road and building projects.

Finally, we would like to forward our deepest gratitude and respect for all staff members and workers for their contribution and dedication towards the success of the company.

Happy and Prosperous New Year!!

# 3 ከልዩ እንግዳችን ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ
## Interview with Our Special Guest



**ወ/ሮ ፀሐይ ወ/ሰንበት**
የፊንጫ ፏፏቴ ደረቅ ጭነት ማመላለሻ ኃላ/የተ/የግል ማህበር ሥራ አሥኪያጅ
**Mrs. Tsehay W/Senbet**
General Manager, Finchaa Fuafuate Freight Transport Plc.

በዓለማችን በተለያዩ የሥራ ዘርፎች ላይ ተሰማርተው ባደረጉት ጥረት ስኬታማ መሆን የቻሉ የሣይንስ ፣ የንግድ ፣ የፈጠራ እና የኪነ-ጥበብ ፈርጦች ታይተዋል። ከነዚህ መካከል በሀገራችን ውጤታማ የሆኑ ሀገር በቀል የኩባንያ መሥራቾችና ባለቤቶች አሉ።

የዚህ ቃለ ምልልስ እንግዳችን የገበኮን ኃ/የተ/የግል ኩባንያ ባለ አክሲዮን እና የኩባንያው ዋና ሥራ አሥኪያጅ የሆኑት የአቶ ገምሹ በየነ ባለቤት ወ/ሮ ፀሐይ ወ/ሰንበት ናቸው።

ወ/ሮ ፀሐይ ከባለቤታቸው ከአቶ ገምሹ ጋር በመሆን በሥራ የሚያምን ጠንካራና ታታሪ ቤተሰብ በመመስረት ከትንሽ ደረጃ ተነስተው በጥረት ኩባንያውን ከፍተኛ ደረጃ የማድረስ እና የመምራት ተምሣሌታዊ ታሪክ አላቸዉ።

ከኩባንያው ጋር የተያያዙ የሥራና ሌሎች ግላዊ ፣ ቤተሰባዊ እንዲሁም ማህበራዊ ህይወታቸውን በተመለከተ ከወ/ሮ ፀሐይ ጋር ቆይታ አድርገናል። መልካም ንባብ።

The world has shown us different personalities who become successful over the course of their hard work from all walks of life and fields of commitment such as science, commerce, arts and many other. Likewise, here we have individuals who able to make commendable history.

Our guest is Mrs. Tsehay Wolde-Senbet, Co-Owner of GEBECON Plc and also wife of Mr. Gemshu Beyene, the General Manager of the Company.

Mrs. Tsehay has proven the possibility of making ones dream true through hard-work. She has an exemplary life from the start as she established a very dedicated and diligent family with Mr. Gemshu.

Mrs. Tsehay shares her time-honored personal and social life as a wife, as a mother and her expertise as Co-owner of the company. Good Reading!

ወ/ሮ ፀሐይ ጥሪያችንን አክብረዉ ለዚህ ቃለ መጠይቅ ፈቃደኛ ስለሆኑ በራሴ እና በድርጅቱ ስም እጅግ አመሰግናለሁ፡፡

**ወ/ሮ ፀሐይ፡** እኔም እንግዳ አድርጋችሁ ስለጋበዛችሁኝ እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ፡፡

**ጥያቄ፡** ሥራ ለእርስዎ ምንድነው?

Mrs. Tsehay, First of all I would like to thank you for your time for this interview – it's an honor.

**Mrs. Tsehay:** I also thank you for welcoming me for this.

**Q.** What does work means for you?

**Mrs. Tsehay:** I believe that the existence of human kinds and work are two faces of same coin. In order

ወ/ሮ ፀሐይ፡ መኖር እና መሥራት የማይነጣጠሉ የአንድ ሣንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸው፡፡ የሰው ልጅ ለመኖር መሥራት ይኖርበታል፡፡ መታወቅ ያለበት ግን የምንሠራው ሥራ ለራሳችን ለመኖር ብቻ መሆን እንደሌለበት ነው ይልቁንም የምንሠራው ነገር ከራሳችን አልፎ ለህብረተሰብ ፣ ለሀገር ፣ ለሰው ልጆች ጠቃሚ መሆን አለበት፡፡ በአጠቃላይ መሥራት የአማራጭ ጉዳይ ሳይሆን ሥራ ለዕድገት ዋናዉ መሠረት እና ግዴታም ነው፡፡

ጥያቄ፡ የሥራ ድርሻዎትን ቢነግሩን?

ወ/ሮ ፀሐይ፡ የገበኮን እህት ኩባንያ የሆነው የፊንጫ ፏፏቴ ደረቅ ጭነት ማመላለሻ ኃላ/የተ/የግል ማህበር ዋና  ሥራ አሥኪያጅ እና ባለአክሲዮን ነኝ፡፡

ጥያቄ፡ ለገምሹ በየነ ኮንስትራክሽን ኃላ/የተ/የግል ኩባንያ መፈጠር ዋና ምክንያቶች ምንድናቸው?

ወ/ሮ ፀሐይ፡ ለገበኮን መፈጠር ብዙ ምክንያቶች ቢኖሩም ዋናው ምክንያት ግን የባለቤቴ የአቶ ገምሹ በየነ የሥራ ፍቅር እና ሥራን ትንሽ እና ትልቅ ሳይል መሥራት መቻሉ ነው፡፡ ከዚያ ቀጥሎ የዚሁ የሥራ መውደድ ዉጤት የሆነው የፊንጫ ፏፏቴ ደረቅ ጭነት ማመላለሻ ኃላ/የተ/የግል ማህበር ነው፡፡ ድርጅቱ ለዛሬው ገበኮን መሰረት የተጣለበትን ሥራ አሥተምሮን ጥሩ ልምድ የቀሰምንበት እንዲሁም ገንዘብ ያፈራንበት ድርጅት ነው፡፡ በአጭሩ ፊንጫ ፏፏቴ ደረቅ ጭነት ማመላለሽ ኃላ/የተ/የግል ማህበር ለገበኮን የጀርባ አጥንት ነዉ፡፡

ጥያቄ፡ ቀደም ባለው ጊዜ ሰዎች ንግድን በዘልማድ እንጂ በተደራጀ መልኩ ሲሰሩ የተለመደ አልነበረም፡፡ ከመጀመሪያው ድርጅት የማቋቋም ሀሳብ እንዴት መጣ?

ወ/ሮ ፀሐይ፡ ድርጅት የማቋቋም ሀሳብ የመጣዉ ከባለቤቴ ከአቶ ገምሹ በየነ ነው፡፡ ባለቤቴ በጣም ጎበዝ እና ጠንካራ ሰው ነው፡፡ ሥራን በዕቅድ መሥራት ይወዳል ፤ ሩቅ አሳቢ እና ባለራዕይ ነው፡፡ በዚያን ጊዜ በብዛት እንደሚታየው በዘልማዳዊ አካሄድ ያለ ዕቅድ ዝም ብለን ሄደን ቢሆን ኖሮ በመንገድ ላይ እንቀር ነበር፡፡ ነገር ግን ባለቤቴ በህግና በተጠና አካሔድ በጣም ያምናል፡፡ ነገሮችን ሰው አደረገ ብሎ ሳይሆን በልዩነት በመሥራት እና አጠንክሮ በመያዝ በሚገባ በማከናወን ያምናል፡፡ ከሁሉም በላይ ግን እዚህ ለመድረሳችን የእግዝአብሐር ፈቃድ ነው፡፡ እሱ በሥራችን ሁሉ ከእኛ ጋር ስለሆነ ለዛሬዉ ቀን እና ስኬት በቅተናል፡፡ ደግሜ እግዚአብሔርን ላመሰግን እወዳለሁ፡፡

ጥያቄ፡ ለገበኮን ስኬታማነት ዋና ዋና ምክንያቶች ምንድን ናቸው?

ወ/ሮ ፀሐይ፡ አንደኛዉ እና ትልቁ ምክንያት የድርጅቱ ሠራተኞች ናቸው፡፡ የድርጅቱ ሠራተኞች ድርጅቱን እንደራሳቸው ድርጅት ነው የሚመለከቱት ፤ እነሱ ድርጅቱን እዚህ ለማድረስ ውድ ዋጋ ከፍለዋል። ባለቤቴም እንዴት አድርጎ ከሰው ጋር መሥራት እንዳለበት ያውቃል። ከድርጅቱ ሰራተኞች ጋር በመመካከር ፣ በመነጋገር እና በመቀራረብ ይሠራል፡፡ ሰዎችን በዕድሜ እና በዕዉቀት ለያይቶ አንዱን አቅርቦ አንዱን

to have life human beings should work. But, one thing that should be clear here is what we are working should not be for our own sake only it should rather have importance for the community, the nation and for human beings at large. Generally, work shouldn't be an issue left as an option, it is a must to take for growth.

Q. What is your current role with the Company?

Mrs. Tsehay: I am the shareholder and General Manager of Fincha Fuafuate Freight Transport Plc.

Q. What was the major motive for establishing GEBECON Plc?

Mrs. Tsehay: Even if there were a lot of reasons to establish GEBECON Plc at first place the diligence of my husband Gemshu Beyene takes foremost of everything. The other reason is Fincha Fuafuate Freight Transport Plc which is also a result of my husband's diligence. We have gained a lot of lessons from this company which has laid the foundation including the finance for the establishment of GEBECON Plc and Fincha has always been backbone to the success of GEBECON Plc.

Q. In previous times most people run businesses in a conventional manner. How did you come up with the idea of establishing a structured company?

Mrs. Tsehay: The idea of establishing a company initially came from my husband. My husband is very determined and he is a visionary who work with plans. If we followed traditional practices without proper planning and management, we would have been failed by now. My husband believes in rules. He doesn't take things merely for others have taken it. Rather he put his commitment on it. Above all, God helped us reach here. God is always with us in all our activities and successes that we are grateful.

Q. What are the core factors behind the success of GEBECON Plc?

Mrs. Tsehay: Employees of the company take the lead. They consider the company as their own and they toiled a lot in bringing the company this far and at the same time my husband is also well aware how to work with people. He consults and creates sense of cooperation and ownership among employees. He has respect for everyone and never favors one over the other. They also had trust on the progress of the company and the company also benefits its employees through bonus from its profit earning every year. Those employees who have better performance also get recognized at the annual staff

አያርቅም። ለሁሉም ሠራተኞቹ ክብር አለው፡፡ ከሁሉም ጋር ተግባብቶ ይሠራል። አብሮ በመሥራት ከትንሽ ጀምሮ ትልቅ እንደሚኮን አምነውበት በመሥራታቸው ሠራተኞቹ ለዕድገቱ ምክንያቶች ናቸው፡፡ ድርጅቱ ከሚያገኛቸው ትርፎችም ሠራተኞቹ ተጠቃሚ ናቸው፡፡ ድርጅቱ በዓመት ከሚያገኘዉ ለሠራተኞቹ ቦነስ ይሰጣል፡፡ የበለጠ የሥራ ዉጤት ያመጡት በጠቅላላዉ የሠራተኞች ዓመታዊ ስብሰባ ፊት ይሸለማሉ፡፡

ሌላው ምክንያት ሥራን የመገምገም ስርዓታችን ነው፡፡ በዚህ አሠራር አቶ ገምሹን ጨምሮ ሁሉም ሠራተኞች የሥራ አሠራር እና አፈጻጸም እኩል ይገመገማል፡፡ በዓመታዊ የሠራተኞች ጉባኤ ላይም ጥሩ ተሞክሮዎች ይቀመሩበታል፡፡ የላቀ ውጤት ያስመዘገቡ ሠራተኞች እና ፕሮጀክቶች ልዩ ሽልማት ያገኛሉ፡፡ ይህ ተሞክሮ ደግሞ በየጊዜዉ የሠራተኞቻችንን የሥራ ወኔ እና ተነሳሽነት ክፍ ሲያረግ ኖሯል፡፡

ሌላው ደግሞ የምንከተለው የሥራ አሠራር ዘመናዊ መሆን ነው። የምንጠቀምባቸዉ መሣሪያዎች አዳዲስ እና በሥራው ዓለም የተመሠከረላቸዉ ብራንድ ናቸው፡፡ እነዚህ አዳዲስ ማሽኖች ለሥራም ሆነ ለማሥተዳደር አመቺ ናቸው፡፡

በተጨማሪም ሠራተኞችን የማብቃት ፖሊሲያችን ለድርጅቱም ሆነ ለሠራተኞች ሁለንተናዊ ዕድገት ከፍተኛ አስተዋፅኦ አበርክቷል፡፡

ጥያቄ፡ እስቲ ደግሞ ወደ ቤተሰብ ኑሮ ልመልስዎትና አቶ ገምሹ በትዳራቸዉ ምን አይነት ሰዉ ናቸዉ?

ወ/ሮ ፀሐይ፡ ርህሩህ ፣ ለሰዉ አዛኝ ፣ ቤተሰቡን የሚወድ ፣ የታመመን ሰው ዝም ብሎ ማለፍ የማይችል ለትዳሩም አሳቢ ጠንካራና ታታሪ ሰዉ ነው፡፡

ጥያቄ፡ አቶ ገምሹ ጠዋት ወደ ሥራ ሲሄዱ እና ማታ ከሥራ ወደ ቤት ሲመለሱ ቤተሰቡ ውስጥ ያለው ድባብ እንዴት ነው?

ወ/ሮ ፀሐይ፡ ማታ ከሥራ ሲመለስ ገና የመኪናውን ድምጽ ኢሉ (ኢሊሊ ሴት ልጃቸው) ስትሰማ በሩጫ ወጥታ ትቀበለዋለች፡፡ ወደ ቤት ሲገባ የሚቀይረውን ልብስ እንሰጠዋለን፡፡ በፍቅር ተቀብለን ከሻወር መልስ ቀለል ያለ ምግብ እንሰጠዋለን፡፡ እረፍት ከወሰደ በኋላ እኔ ደግሞ እሱ የሚወደዉን ምግብ ስለማውቅ አዘጋጅተን ስለምንቆየው እናቀርብለታለን። በዚህ መልክ ከመላ ቤተሰቡ ጋር ሲጫወት ያመሻል፡፡

ጥያቄ፡ የአቶ ገምሹ የፕሮቶኮል ጉዳይ ተጠሪ ማን ነው?

ወ/ሮ ፀሐይ፡ (ረዥም ሳቅ...) የሱን የፕሮቶኮል ጉዳይ በልዩነት የምከታተለዉ እኔ ነኝ፡፡ ባለቤቴ አምሮበት ወደ ሥራው እና ወደ እንግዶቹ እንዲሄድ እፈልጋለሁ፡፡

ጥያቄ፡ አቶ ገምሹ በጣም የሚወዱት ምግብ ምንድን ነው?

assembly meeting. Both best performing employees and projects are recognized and get awards. This has been increasing the commitment of our employees.

The other source of our success is our culture of evaluation. In this regard, everybody's performance including Mr. Gemshu will be evaluated in the same way. Past experiences get booked during the annual staff assembly meeting.

The other factor is the efficient methods that we are working with. The machineries we are using these days are well recognized brands in the industry. Such kinds of machineries are good both for the general work as well as to administer projects.

In addition to that, the capacity building policy we have in our company also helped for all rounded progress of our employees.

Q. Let me take you to family affairs. What kind of person is Mr. Gemshu at home?

Mrs. Tsehay: He truly loves his family. He is committed both for his work and he knows how to take care of his family. Given his compassionate nature, he always wants to help patients wherever he see sick persons.

Q. Tell us about the vibe in your family while Mr. Gemshu is at home?

Mrs. Tsehay: The moment he arrive home; whenever Elu (Elilly is their daughter) catches the beeps of his car she run out to receive him and she escort him into the house. He then dress-up pajamas and take simple meal. Usually, I prepare his favorite meal and he spends the night enjoying with the whole family.

Q. Who take care of Mr. Gemshu's protocol affairs?

Mrs. Tsehay: (long laughter...) actually it's me who take care of his protocol. I want my husband to look great and gentle whenever he goes to work or to meet his guests.

Q. What type of food does Mr. Gemshu prefers most?

Mrs. Tsehay: (laughter...) you know what, he doesn't, in fact he prefers a well prepared 'Shiro wot'.

Q. It was during the inaugural ceremony of Elilly International Hotel that the Master of the Ceremony (MC) asked Mr. Gemshu about his favorite food and he responded that he prefers 'Shiro wot' and the MC said 'why is this all hard-work just for Shiro' (Shiro wot is assumed to be commoners food in Ethiopia). Is this also true?

ወ/ሮ ፀሐይ፡ (ሳቅ...) እሱ የሚወደው ጥሩ ሽሮ ነው፡፡

ጥያቄ፡ አንድ ጊዜ አርቲስት ሰራዊት ፍቅሬ ይመስለኛል በኢሊሊ ኢንተርናሽናል ሆቴል የምረቃ ፕሮግራም ላይ አቶ ገምሹ ምን እንደሚወዱ ጠይቆአቸዉ እሳቸውም ሽሮ እወዳለሁ ብለዉ ሲመልሱለት 'ይኼ ሁሉ ልፋት ሽሮ ለመብላት' ብሎ ነበር አሉ እዉነት ነዉ?

ወ/ሮ ፀሐይ፡ (ሳቅ...) አዎ እንደዛ ብሎ ነበር ፤ ግን እሱ የሚሠራው ለተሸለ የምግብ ፍላጎት አይደለም፡፡ ለዕድገት ነው፡፡ ሰዎች ድርጅቱ ውስጥ ሠርተው እንዲኖሩ ፣ በሀገር ዕድገት ውስጥ የራሱን ሚና በመጫወት ለውጥ ለማምጣት ነው፡፡ ይህ ነው ፍላጎቱ፡፡

ጥያቄ፡ እስቲ ወደ ኋላ ልመልስዎትና ለዛሬው ውጤታማነታችሁ ምክንያት የሆኑትን የቤተሰብ የሥራ ባህሪ ይንገሩን?

ወ/ሮ ፀሐይ፡ እዚህ ደረጃ ስንደርስ ከትንሽ ተነስተን ማደግ እንደምንችል እምነት ነበረን፡፡ በከፍተኛ ደረጃ ሥራ በመውደዳችን ቤተሰባችን ሥራን ሳይንቅ በመሥራቱ ፣ መተጋገዛችን ፣ መተሳሰባችን እንዲሁም በነገሮች ላይ ተመካክረን እና ተነጋግረን መግባባታችን ለዛሬው ስኬታማነታችን ከፍተኛ አስተዋፅኦ ነበረው ብዬ አምናለሁ፡፡

ጥያቄ፡ ከአንድ ውጤታማ ወንድ በስተጀርባ አንዲት ጠንካራ ሴት አለች የሚል ዓለም አቀፋዊ እውቅና ያለዉ አባባል አለ፡፡ ይህ አባባል ከእርሶ እና ከአቶ ገምሹ ጋር ያለዉ ተምሣሌት እንዴት እንደሆነ ቢነግሩን?

ወ/ሮ ፀሐይ፡ መጀመሪያ ስንገናኝ የነበረን ፍቅር ብቻ ነው፡፡ ግን ሁሉንም ነገር በሥራ ማግኘት እንደምንችል ሙሉ እምነት ነበረን፡፡ በዚህ ተስፋ ነበር የህይወት ጉዞአችንን አንድ ብለን የጀመርነዉ፡፡ ያኔ እሱ እየወጣ የመስክ ሥራ ሲሰራ እኔ ደግሞ እዚህ የነበረውን እሱ የሚሰጠኝን ሥራ በደንብ በመሥራት ፤ እሱ የሚለኝን በመስማት እኔ በማቀርበው ሀሳብ ላይ ደግሞ እሱ በመስማማት ፣ በመተጋገዝ እና በመረዳዳት እንዲሁም አንዳችን ለአንዳችን ባለን ፍቅር ለዛሬው ውጤታማነታችን በቅተናል፡፡

ጥያቄ፡ ስለዚህ ይህንን ዓለም አቀፋዊ አባባል ተወጥቼዋለሁ ነዉ የሚሉት?

ወ/ሮ ፀሐይ፡ እሱን በማገዝ ረገድ አንድም ጊዜ ስለማልሰንፍ ትክክለኛ አስተዋፅኦ እና ትልቅ ቁርጠኝነት አለኝ ብዬ አምናለሁ፡፡

ጥያቄ፡ አዎ! በሚገባ ተወጥቼዋለሁ ብዬ አምናለሁ፡፡

ጥያቄ፡ በእርሶ እይታ የአቶ ገምሹን ልዩ ችሎታ ምንድነው?

ወ/ሮ ፀሐይ፡ ሥራ ወዳድነቱና የሥራ ፈጠራ ችሎታው ፣ ከሰው ጋር የመሥራት ችሎታው ፣ ሩቅ አሳቢነቱ እና የያዘዉን ሳይተገብር የማይመለስ መሆኑ፡፡

ጥያቄ፡ ከሥራ ውጭ ባለቤትዎን ምን ያስደስታቸዋል?

ወ/ሮ ፀሐይ፡ የታመመን ሰው መጠየቅ እና መርዳት ይወዳል፡፡ ታሞ

Mrs. Tsehay: (laughter...) Yeah, the MC said so. But here what I would say is that my husband is just working hard not to serve himself the best meal of any kind. His ultimate purpose is rather to provide work opportunity for people and to have his role in the development of the country.

Q. What was the work culture that has influence in your today's endeavor in the family?

Mrs. Tsehay: We had strong believes that we would reach to this stage from the very scratch. I believe the hard work habit beside collaboration we have had among each other have contributed to our success.

Q. Please tell us about what the long-standing universal say that, behind every successful man, there is a strong, wise and hardworking woman, has between you and Mr. Gemshu.

Mrs. Tsehay: When we met at the start what we had was only love. But, we believe that we will get everything through hard work. It was with this hope that we started life together. At that time, he often travels to field work while I manage the task he had given me here. I respect his ideas and he also takes my opinions. With the love we have for each other we have been working in strong cooperation which helped us reaching to this stage.

Q. Therefore, you're saying that you best served this saying?

Mrs. Tsehay: To tell you that I have never been exhausted to support my husband and I believe I dedicated myself to the best of my capacity. Indeed! I exactly met that saying.

Q. What is exceptional about Mr. Gemshu?

Mrs. Tsehay: His dedication, creativity, vision and determination about his task. He has integrity to everyone.

Q. How does your husband spend his leisure time other than work?

Mrs. Tsehay: He usually visits patients. He never leave a patient without getting them treated and I always praise him for having such heart.

Q. How do you manage work, family and other social life issues?

Mrs. Tsehay: When it comes to the work, my husband manages most of the tasks and I have role in

የተቸገረ ሰዉ ካየ ዝም ብሎ ማለፍ አይችልም ፤ ያሳክማል እኔም ይህንን ተግባሩን በጣም አደንቀዋለሁ፡፡

**ጥያቄ፡** ሥራን ፣ የቤተሰብ ኃላፊነትንና ማህበራዊ ኑሮን እንዴት ያቻችሉታል?

**ወ/ሮ ፀሐይ፡** ሥራን በተመለከተ ባለቤቴ በበላይነት ሲመራ እኔም እሱን የማገዙን ሚና እወጣለሁ፡፡ ቤቴሰብ እና ማህበራዊ ኑሮን ደግሞ በበላይነት መያዙ የእኔ ድርሻ ሲሆኑ እሱም ጊዜ ሲኖረዉ ይረዳኛል፡፡ ሁለቱንም በማቻቻል እየተረዳዳን እንሠራለን፡፡

**ጥያቄ፡** ለእርስዎ ተምሣሌት ወይም ሮል ሞዴልዎ ማነው?

**ወ/ሮ ፀሐይ፡** ለእኔ መተኪያ የሌለዉ አርአያዬ ባለቤቴ ነው፡፡ እሱ ለእኔ የትዳር አጋር ብቻ ሳይሆን አስተማሪዬም ጭምር ነዉ፡፡ ከትንሽ ተነስቶ ትልቅ ደረጃ መድረስ እንደሚቻል ሠርቶ ያሳየኝ ፣ ያስተማረኝ ጀግናዬ ነው፡፡ ነገሮችን በጥልቀት የመመርመር ችሎታው ከፍተኛ ነው፡፡ የህይወት መርህ ይሆናል ብሎ የሚያምንበትን መርቶ ከግብ የሚያደርስ መንፈሰ ጠንካራ ሰው ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም አይፈራም ፣ ማንኛውም ነገር ይሆናል ብሎ የሚያምን የሥራ ፈጠራ ባለቤት ነው፡፡ ለዚህ አርአያዬ ገምሹ ነው፡፡

**ጥያቄ፡** በዓለማችን የሚያደንቁት ተቋም የትኛው ነው? ለምን?

**ወ/ሮ ፀሐይ፡** ከዓለማችን የማደንቀው ድርጅት የበጎ አድራጎት ድርጅትን ነው፡፡ ምክንያቱም ሰውን ከመርዳት እና ከማዳን የበለጠ ምን የሚያስደስት ነገር አለ? እግዚአብሔር ካለ እኔም ለወደፊት የራሴ የበጎ አድራጎት ድርጅት የማቋቋም ዓላማ አለኝ፡፡ እግዚአብሔር እንደሚረዳኝም እምነቴ ነው፡፡

**ጥያቄ፡** ገበኮን ከዛሬ አሥር ዓመት በፊት የት ነበር? ከአሥር ዓመት በኋላስ የት እንጠብቀው?

**ወ/ሮ ፀሐይ፡** ገበኮን ከዛሬ አሥር ዓመት በፊት የንግድ ፍቃድ ነበር ያወጣነዉ፡፡ በትልቅ ራዕይ እና በትንሽ ደረጃ ላይ ነበር፡፡ እግዚአብሔርም ረድቶን ራዕያችንን ማሳካት ችለናል፡፡ ከአሥር ዓመት በኋላ ደግሞ እግዚአብሔር ካለ ዓለም አቀፍ ድርጅት ይሆናል ብዬ አምናለሁ፡፡

**ጥያቄ፡** በህይወትዎ በጣም ደስ ያለዎት ቀን መቼ ነው?

**ወ/ሮ ፀሐይ፡** ኢሊሊ ልጄን የወለድኩባት ቀን ናት፡፡ ልጅ የእግዚአብሔር በረከት ነው፡፡ እኔና አባቷ ኢሉን ያገኘን እለት ደስታችን ወደር አልነበረዉም፡፡ በጣም ደስ ብሎን ነበር፡፡ እግዚአብሔር ክብሩ ይስፋና፡፡

**ጥያቄ፡** ለነበረን ጊዜ እጅግ አድርጌ አመሰግናሁ፡፡

**ወ/ሮ ፀሐይ፡** እኔም አመሰግናለሁ፡፡

supporting him and mostly I look after our family as well as the social life. But we both take care of such things together.

Q. Who is your role model?

Mrs. Tsehay: My husband is an exceptional role model. For me, he is not only a husband but also a teacher. He is my hero who has proven that change can start from lower status. He has the skill to see things in depth. He is strong minded person presenting himself in principle of life. For such reasons, he doesn't afraid of creating new things and that is also I am saying Gemshu is my role model.

Q. What kind of organization do you admire most and why?

Mrs. Tsehay: I really admire humanitarian organizations. Because I don't see if there is anything worth more than helping and curing people? – God's willing, I also want to establish a humanitarian organization in the future. I believe God will help me achieve my dream.

Q. Where was GEBECON Plc ten years before and where will we see it in coming ten years from now?

Mrs. Tsehay: Ten years before GEBECON Plc had only a license. It was a company with big vision at smaller level. With the help of God we have been able to achieve our dream. I am optimistic that in the coming ten years, it will also become an international company.

Q. When was the happiest moment in your life?

Mrs. Tsehay: It was a day I gave birth to my daughter Elilly. I believe, child is God's gift. That time, I and Gemshu were so excited for God has given us an adorable child like her. Thanks to God!

Thank you very much.

Mrs. Tsehay: Thank you!

## የቁርጥ ቀን ልጅ

ከየክልላቱ ተሰባስቦ ወጣት
በገምሹ በየነ በሀገር ልጅ ባለሀብት
ሁሉም በየሙያው በመጣበት እውቀት
ዛሬ ደርሷል ይሄው መንገዱን በመሥራት

እናም ወንድም ንቃ ይፅና መሠረትህ
ይህንን ድርጅት ለአለም አሳውቀህ
በሥራ ጊዜህን በአግባቡ ተጠቅመህ
ስምህን አስጠራው በሚያኮራው ሙያህ
እሱም እንዲሸለም አንተም ተደስተህ

ለማይ-ፀብሪ ዲማ ከዚያም ፍየል-ውሃን በጊዜ ጨረስክ
ለአሰሪህ አሰሪ ለአውራው ጎዳና በውል እንዳስረከብክ |
ሰሜን ሸዋ ጎንደር ሐረርን ጨምሮ
ከተሠጠው እቅድ ሪከርዱን ሰባብሮ
አይሶ ተሸላሚ በጥራት ኤጀንሲ
በውሽክልክል ሥራ ሳይሆን ተሃያሲ

በተቀጠርክበት ጠንክረህ በሙያህ
የቁርጥ ቀን ልጅ ሁን አንተም ተሸልመህ
ድርጅቱም ይሁን ስመጥር ገናና
ድንበር ተሻጋሪ እንደቱርክ ቻይና፡፡

## እኔ ምን ቸገረኝ

ባልሠራሁት ሀጥያት ስም ቢሠይሙልኝ
ከቶ በማላውቀው ጠልቶ ቢኮንነኝ
ማማት ሱስ ሆኖበት ሁሌ ቢዘክረኝ
በአፍ እያነሳ በእጁ ቢጥለኝ
እሱን ካልከበደው እኔ ምን ቸገረኝ፡፡

## ወርቃማ አባባሎች

- ተግባር የሌለው ራዕይ የቀን ቅዠት ነው፤ራዕይ የሌለው ተግባር አደጋ ነው፡፡
- ራስን መውቀስና መታዘብ ለመሻሻል የመጀመሪያ እርምጃ ነው፡፡
- አመሳክሮ መነሳት ከሀፍረት ያድናል፡፡
- መልካም ግንኙነት የስኬትና የብልፅግና ጎዳና ነው፡፡

ከሚፍታ መሀመድ



Gebecon PLC Management Team

# 4 የገበኮን ዕድገት ምልከታ
# Tracking the Growth of the Company

ከዚህ በታች በግራፉ እንደተመለከተው ድርጅቱ ከተቋቋመ ጊዜ ጀምሮ በገንዘብ፣ በፕሮጀክት እና በሰራተኞች ብዛት አመርቂ እድገት አሳይቷል። ይሄም አመርቂ ውጤት ሊመዘገብ የቻለው ማኔጅመንቱ እና ሠራተኛው የድርጅቱን ተልዕኮና አላማ ለማሳካት ያደረጉት ያላሰለሰ ጥረት ውጤት ነው።

As depicted below, there has been a steady growth in the company's financial position, number of projects and employees since its establishment. The fast growth attained by the company over the last eight years is depicted as follows. Such fast growth is attributed to the strong commitment of the management and employees in the realization of the company's mission and goals.

**Total Revenue in Birr ('Million)**




**Gross Profit in Birr ('Million)**




**Net Income in Birr ('Million)**




**Total Assets in Birr ('Million)**




**Fixed Asset (Net) in Birr ('Million)**




**Total Net Worth in Birr ('Million)**



# OVER THE LAST 8 YEARS

GEBECON PLC registered a record high average growth rates.

| | | | |
|---|---|---|---|
| 54% TOTAL REVENUE | 46% CAPITAL (Net Worth) | 37% FIXED ASSET | 48% TOTAL ASSET |
| 49% PBT | 31% ROE | 27% EMPLOYEES | |

2000 E.C — 2007 E.C

## Net Profit Margin in %




## Gross Profit Margin from Operation in %




## Return on Equity (ROE) in %




## Return on Asset (ROA) in %




## Value of Work at Hand in Birr ('Billion)



# 5 ዓመታዊ የኩባንያው ፕሮጀክቶች አፈጻጸም
# Company Annual Project Performance



**ኢንጂነር ፍቃዱ አበራ**
የኮንስትራክሽን ሥራ ዳይሬክተር
**Eng. Fekadu Abera,**
Director, Construction Works Dep't

ብዙ አስተዳደራዊ እና ቴክኒካዊ ተግዳሮቶች ቢያጋጥሙትም ድርጅታችን በ2008 ዓ.ም በጀት ዓመት ካቀደው የሥራ ክንውን ዕቅድ ውስጥ ከ87% (መቶኛ) በላይ አሳክቷል፡፡

በ2008 በጀት ዓመት ውስጥ ካጋጠሙን ትላልቅ ተግዳሮቶች መካከል የትክክለኛ ዲዛይን እጥረት፣ በቂ ያልሆነና ዘግይቶ የሚቀርብ ዲዛይን፣ የወሰን ማስከበርና የካሳ ክፍያ በወቅቱ አለመፈታት በዲዛይን መቀየር እና መሻሻል ምክንያት የሚቀያየር የሥራ ይዘት ሲሆን ከዚሁ ጋር ያልተጠበቀ የስራ ጫናና ያልተጠበቀ ሥራ የመጨመር ሁኔታ ታይቷል፡፡ ለምሳሌ በሐረር ባይ ፓስ አስፋልት መንገድ ሥራ ፕሮጀክት በጣም ትላልቅ የሆኑ የቋጥኝ ወይም የአለት ቁፋሮ ሥራ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ እነዚህ እንቅፋቶች ጥቅጥቅ ያለ መንደር እና ከተማ አካባቢ በሚሆኑበት ወቅት ትልቅ ችግር ፈጥረውብናል፡፡ ለዚህ ትልቅ ምሳሌ የሚሆነው የሐረር ባይ ፓስ የመንገድ ስራ ፕሮጀክት ነው፡፡

ድርጅታችን በ2008 በጀት ዓመት በአጠቃላይ ሰባት የመንገድ እና የህንፃ ግንባታ ፕሮጀክቶች ላይ ሲሠራ ነበር ፡፡ እነዚህም ፡-

- ዲማ ፍየል ውሃ የአስፋልት መንገድ ሥራ ፕሮጀክት (ደንበኛ -ኢመባ)
- ኪ.ሜ 72 ዓለም ከተማ አስፋልት መንገድ ስራ ፕሮጀክት (ደንበኛ - ኢመባ)
- አዘዞ -ጎርጎራ የመንገድ ደረጃ ማሻሻያ አስፋልት መንገድ ሥራ ፕሮጀክት (ደንበኛ - ኢመባ)
- ሐረር ባይ ፓስ አስፋልት መንገድ ሥራ ፕሮጀክት (ደንበኛ - ኢመባ)
- የኢሊሊ ኢንተርናሽናል ሁለገብ ህንፃ ግንባታ

Despite enormous administrative and technical challenges, the Company has maintained its success record through achieving over 87% of the target plan in 2015/16 (2008 E.C).

In 2015/16, the major challenges faced among other include lack of sound design, insufficient and late design provisions, untimely removal of ROW obstructions, varied work items merely arising from frequent design amendments and improvements. Besides an unanticipated work load and scope of work like huge rock excavation were encountered in urban areas (like Harar-By-Pass Road Project).

The company was running a total of seven road and building projects during the fiscal year under review. They include:

- Dima- Feyel Weha Asphalt Road Project (Client – ERA);
- Km72 -Alemketema Asphalt Road Project (Client – ERA);
- Azezo-Gorgora Road Upgrading Asphalt Road Project (Client – ERA);
- Harar-By-Pass Asphalt Road Project (Client – ERA);
- Multipurpose Building Complex Project (Client – Elilly International Hotel)

- የአምቦ ከተማ የውስጥ ለውስጥ የአስፋልት መንገድ ሥራ ፕሮጀክት (ደንበኛ ኢ.መባ)

- የአርሲ ዩኒቨርሲቲ የህንፃ ግንባታ ናቸው፡፡

እንደሚታወቀው የዲማ ፍየል ውሃ የአስፋልት መንገድ ፕሮጀክት ሥራ ከተያዘለት ጊዜ በፊት ስድስት ወር አስቀድሞ በ2007 ዓ.ም ማለቁ ይታወሳል፡፡ ይሁን እንጂ በኮንትራት ውሉ መሠረት የመንገድ ሥራ ፕሮጀክቱን ደንበኛው ሙሉ በሙሉ የተረከበው በዚህ ዓመት ሚያዝያ 2008 ዓ.ም ነው፡፡

የተቀሩት እንደ አዘዞ-ጎርጎራ፣ ኪ.ሜትር 72 ዓለም ከተማ፣ ሐረር ባይ ፓስ ፣ ኢሊሊ ኢንተርናሽናል ሆቴል የህንፃ ግንባታ ፕሮጀክት እስከ በጀት ዓመቱ ማለቂያ ጊዜ ድረስ ሲሰሩ የነበሩ ሲሆን የአርሲ ዩኒቨርስቲ የህንፃ ግንባታ እና የአምቦ ከተማ የውስጥ ለውስጥ የአስፋልት መንገድ ሥራ ፕሮጀክቶች ገና አዲስ የተጀመሩ ናቸው፡፡

ከዚህ በታች የሠፈረው ግራፍ የታቀደውን ጠቅላላ ዕቅድ እና በትክክል የተተገበረውን የድርጅቱን የበጀት ዓመቱን ሥራ ጨምቆ የሚያሳይ ነው፡፤

- Ambo Town Aspahlt Project (Client – ORA) and

- Arsi University Building Project (Client – Arsi University)

It was recalled that Dima- Feyel Weha Asphalt Road Project had successfully been completed in 2015 (2007 E.C) six months ahead of the contract period. However, due to contractual reasons, the road project was completely transferred to the client this year in April 2016 (2008 E.C.)

While projects like Azezo-Gorgora, Km72-Almketama, Harar-By-Pass and Elilly International Hotel Multipurpose Building Project were among the active projects in the fiscal year just ended, Ambo Town Asphalt Road project and Arsi University Building project were among the newly acquired ones at the end of this fiscal year.

The figure below summarizes the aggregate planned and actual accomplishments of Company projects during the fiscal year.




Figure 1: Overall Project Plan Vs Actual Accomplishment

ቀጥሎ ያለው ግራፍ ደግሞ የኤስ ቅርፅን በመጠቀም ጠቅላላ ፕሮጀክቶቹን የሥራ ዕቅድ እና በትክክል የተከናወነውን የፕሮጀክቶቹን የስራ ውጤትን አገናዝቦ የሚያሳይ ነው፡፡

The figure below, using s-curve, summarizes the cumulative planned and actual accomplishments of company projects during the reporting period.




Figure 2: S-Curve showing trends of project work progress throughout the year 2007 E.C

ድርጅቱ በበጀት ዓመቱ ሊሠራ አቅዶት ከነበረው ብር 739 ሚሊዮን ውስጥ ከ87% በላይ አሳክቷል፡፡ በዚሁ መሠረት ደግሞ እያንዳንዱ ፕሮጀክት ያስገኘው ገንዘብ እና የነበረው አስተዋፅኦ በቅደም ተከተል በሚከተለው ማሳያ ግራፍ ተመልክቷል፡፡

The Company achieved 87 percent of Birr 739 million it planned during the reporting period. The financial achievements and the contributions of the respective projects is shown in the figure below.




Figure 3: Financial Achievements and Percentage Contributions of the Respective Projects

እነዚህ ሥራ ላይ የነበሩ እና ያሉ የድርጅቱ ፕሮጀክቶች በአማካይ ከ800 በላይ ለሚሆኑ ቋሚ ሠራተኞች እና ከ5000 በላይ ለሚሆኑ ጊዜያዊ ሠራተኞች የስራ ዕድል ፈጥረዋል፡፡ የእያንዳንዱ ፕሮጀክት የሥራ ሂደት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

The undergoing projects had created numerous job opportunities for an average of over 800 permanent employees and 5,000 temporary employees.

The summary of each project progress is presented below:

## 5.1. ዲማ ፍየል ውሃ የአስፋልት መንገድ ስራ ፕሮጀክት

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው የዲማ - ፍየል ውሃ  የመጀመሪያው ጊዜያዊ ርክክብ ከደንበኛው ጋር የተካሄደው በመጋቢት ወር 2007 ዓ.ም ሲሆን በዚያው ተመሣሣይ ዓመት ውስጥ በግልፅ ተመርቋል፡፡ ፕሮጀክቱ ሙሉ በሙሉ ለአሰሪው የተሰጠው የአንድ ዓመት የመጠባበቂያ ጊዜ (One Year Defect Liability Period) ከተጠናቀቀና የሚጠገኑ ነገሮች ተጠግነው እና የተጨመሩ ሥራዎች በሚገባ ተሠርተው ሙሉ በሙሉ በሚያዝያ ወር በ2008 ዓ.ም አስረክበናል፡፡

## 5.2. ኪ.ሜ 72 ዓለም ከተማ አስፋልት መንገድ ስራ ፕሮጀክት

ኪ.ሜትር 72 የመሃል ሜዳ - ዓለም ከተማ የመንገድ ሥራ ፕሮጀክት የሚገኘው በሰሜን ሸዋ ዞን በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ክልል ውስጥ ነው፡፡

ለፕሮጀክቱ ግንባታ ከኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን ጋር ውል የተገባው /የተፈረመው እ.አ.አ ፌብሯሪ 25/2013 ነበር፡፡

የዚህ ፕሮጀክት ሥራ የተመሠረተው በድርብ አስፋልት (Bituminous) የሚሸፈን አዲስ የአስፋልት ሥራ ሆኖ ርዝመቱ 48.3 ኪሜ ሲሆን የDS-4 ጂኦሜትራክ ዲዛይን ደረጃ ያለው ነው፡፡

የፕሮጀክቱ ባህሪይ በትላልቅ ተራራዎች መካከል የሚያቋርጥ፣ ዥው  ያሉ ቁልቁለት እና ቀጥ ያሉ ዳገቶች የሚበዙበት ፣ ከፍተኛ የሆነ የቁፋሮ ሥራ የሚጠይቅ በጣም ረጃጅም የሆኑ የድጋፍ ግንቦች (Retaining Walls) የሚፈልግ እና ድርጅቱ እየሠራቸው ካሉት ፕሮጀክቶች ሁሉ ለየት ያለ የአሠራር ዘዴ የሚሻ ፕሮጀክት ነው፡፡

## 5.1. Dima-Fiyel Weha Asphalt Road Project

As clearly indicated at the outset, the provisional hand over of the project to the client was made in March 2015 following an official inauguration ceremony in the same year .

The road project is fully handed over to the client in April 2016 after one year defect liability period during which defects were maintained and additional works were executed by the Company.

## 5.2. Km72–Alemketema Asphalt Road Project

The Km72-Alemketema Road Project is located in the North Shoa Zone of the Amhara Regional National state. The Contract for the construction of the project was signed with the Ethiopian Roads Authority (ERA) on 25th February, 2013.

The works under this project consists of construction of new Asphalt Double Bituminous Surfacing that covers 48.3 km road with DS-4 geometric design standard.  The project is characterized by traversing mainly through major mountainous, some rolling and very steep escarpment terrain exhibiting the construction of heavy excavation works and several huge retaining structures that requires special work methodology unlike other road projects currently undertaken by the company.







*Partial View of Project Activities at KM72- Alem Ketema Road Project*

በዚህ ፕሮጀክት ካለፉት ዓመታት በተሻለ መልኩ የዲዛይን ጉዳይ ደረጃ በደረጃ በመፈታቱ ካምፓኒው አስፈላጊ የሆኑትን የኮንስትራክሽን ግብአቶች በተሟላ እና የኮንትራት ውሉ በሚፈልገው መሰረት ሥራውን በመሥራት ላይ ይገኛል፡፡

ስለዚህም ፕሮጀክቱ ዋና ችግሩ የነበረው የመሬት መንሸራተት ችግሮች ተለይቶ ታውቆ በመቃለሉ የፕሮጀክቱ አፈፃፀም በአስተማማኝ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ በአሁኑ ጊዜ በፕሮጀክቱ ላይ በጣም ፈታኝ የነበረው የቆረጣ ሥራ እስከ መንገዱ የመጨረሻ መገናኛ ጫፍ ድረስ ተጠናቋል። በመሆኑም በ2009 በጀት ዓመት ተይዘው የነበሩት ዋነኞቹ ሥራዎች ተጠናቀው ያልተጀመሩት ሥራዎች እንደሚጀመሩ ይጠበቃል፡፡

ፕሮጀክቱ አስገባለሁ ብሎ አቅዶት ከነበረው ገቢ 61% ቫትን ጨምሮ ወደ ብር 229 ሚሊዮን ገደማ አሳክቷል፡፡

ከዚህ በታች ያለው አሀዝ የኪ.ሜ 72 - ዓለም ከተማ የመንገድ ስራ ፕሮጀክትን ያለፈው ዓመት ዕቅድ እና አፈፃፀም የሚያሳይ ነው፡፡

Unlike the preceding years, during the reporting fiscal year, the design issues were settled phase by phase thereby enabling the company to fully deploy the resources required to work at full capacity as per the contract requirements.

Thus, it was found and realized that the project is promising in terms of its accomplishments as all critical problems related to sliding were substantially identified and resolved. As of to date, major parts of the excavation work, which has been among the critical activity of the project, has been substantially completed up to the end of the project length. Hence, during the upcoming fiscal year 2016/17, it was planned that major works can be substantially finalized introducing all activities that were not yet commenced.

The project achieved 61 % of its financial plan, which is close to Birr 229 million including VAT, during the year.

The figures below shows Km72-Alemketema Road project Plan Vs Accomplishment.




Figure 4: Plan VS Actual Accomplishment

## 5.3 የአዘዞ ጎርጎራ የመንገድ ሥራ ፕሮጀክት

ይህ ፕሮጀክት በሰሜን ጎንደር ዞን በአማራ ክልላዊ መንግስት ውስጥ የሚገኝ ሲሆን ዋና ሥራው የነበረውን 52.7 ኪ.ሜትር ርዝመት ያለው የጠጠር መንገድ ወደ DBST ደረጃ ከፍ የማድረግ ሥራ ነው፡፡

የመንገዱ ሁኔታ ረጅም የከተማ አካባቢዎችን አቋርጦ የሚሄድ ሲሆን ከአዘዞ-ከተማ መገንጠያ ተነስቶ ቆላድባንና ጨኋይት ከተሞችን ሰንጥቆ በማለፍ ጎርጎራ ከተማ ላይ የሚያበቃ ነው፡፡ መንገዱ በእያንዳንዱ ከተማ አካባቢ 15 ኪ.ሜትር የሚሆን ርዝመት በነጠላ ሽፋን ሲኖረው በአብዛኛው በከተሞች አካባቢ የሚሰሩትን የፍሳሽ (Drainage) ሥራን ጨምሮ የጠቅላላውን ሥራ 45% የያዘ መሆኑ ይታወቃል፡፡

## 5.3. Azezo-Gorgora Upgrading Asphalt Road Project

This project road is located in the Amhara Regional National State in the Northern part of Ethiopia. The work includes upgrading of the existing 52.7 Km gravel road to DBST standard. The project was mainly characterized by intercepting long town sections staring at Azezo town junction to Gorgora and traverses through Kola Diba and Chewit Tows ending at Gorgora Town. The total single lane town section length was estimated to be 15km consisting more than 45% of the total workloads of the project that comprises mainly the construction of town section drainage works.



*Completed 3 Span Girder Bridge*





*Partial View of Completed Asphalt and Sub-base at Azezo Gorgora Road Project*

ለፕሮጀክቱ ሥራ እንቅፋት የሆኑ ችግሮች ቶሎ አለመፈታታቸው በድርጅቱ ሥራ ላይ ከፍተኛ መጓተት አስከትለዋል፡፡ ለምሳሌ የአዘዞ እና የጎርጎራ ከተሞች የወሰን ማስከበር (Row) ሥራ በቅርብ ጊዜ የተፈፀመ እና ሥራው የተለቀቀልን አብዛኛውን ቋሚ ሥራዎቻችንን በከተሞች ውስጥ ልናገባድድ እንችል በነበርንበት በቅርብ ጊዜ ስለሆነ ከፍተኛ ተጽእኖ አሳድሮብናል፡፡

ይህም ሆኖ ሳለ ከላይ ከጠቀስናቸው የከተሞች ቀሪ ሥራዎች በስተቀር የአጠቃላይ ሥራው 90% ማለትም ከ10% በታች ሥራ ሲቀረው በመጪው ጥቅምት ወር 2009 ዓ.ም ወይም ከዚያ በፊት ሙሉው የፕሮጀክቱ ሥራ ይጠናቀቃል ተብሎ ይጠበቃል፡፡

አዘዞ ጎርጎራ የመንገድ ሥራ ፕሮጀክት ሊሠራ አቅዶት ከነበረው ገቢ 75% ቫትን ጨምሮ ብር 264 ሚሊዮን ገደማ ማሳካት ችሎዋል፡፡

Delay in removal of the obstructions majorly affected the company work progress. In this regard, Azezo and Gorgora town section ROW removal was recently completed and hand over was made in order to commence all the permanent activities remaining in the town sections.

However, till the end of this reporting period, except remaining works at the abovementioned town sections, more than 90% of the contract works were completed with the work load remaining less than 10%, which is expected to be substantially completed on or before the end of October, 2016.

Azezo-Gorgora Road project achieved 75 % of its financial plan, which is close to Birr 264 million including VAT during the fiscal year.




Figure 5: Plan VS Actual Accomplishment

## 5.4 ሐረር ባይ ፓስ የአስፋልት መንገድ ስራ ፕሮጀክት

ይህ ፕሮጀክት በሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ክልል ውስጥ የሚገኝ ሆኖ በሐረር ከተማ ዙሪያ የሚሠራ ሲሆን የ20 ኪ.ሜትር ርዝመት ያለው የኮንክሪት አስፋልት መንገድ ሥራ ነው፡፡

ፕሮጀክቱ በየወቅቱ ከሚያጋጥሙት ሥራ የማስቆምና የማቋረጥ ችግሮች እስከ መጨረሻው ድረስ እጅግ የተጎዳ ፕሮጀክት ነው፡፡ በየወቅቱ በአካባቢው ነዋሪዎች በሚነሱ የሥራ ማስቆም ጉዳዮች ሥራው እንደታሰበው ባይሄድም ከህብረተሰቡ ጋር በሚደረግ ውይይት ፣ ከጎሣ መሪዎችና ከአስተዳዳሪዎች በሚደረግልን ድጋፍ ግን ሥራው ተከናውኗል። በእነዚህ እንቅፋቶች ግን የፕሮጀክቱ የሥራ ግስጋሴ በጣሙን ተደናቅፏል።

ከዚህም በተጨማሪ በጣም ከፍተኛ የሆነ የድንጋይ ቁፋሮ እና አካባቢው በጣም የለማ እና ከተማ የሚበዛበት በመሆኑ በፈንጂ ፍንዳታ ወቅት በሰዎች መኖሪያ ቤት እና ተክል ላይ ጉዳት እንዳይደርስ በሚደረገው ጥንቃቄ ሥራውን እንደልብ በነፃነት ስለማይሰራ ፕሮጀክቱን ከባድ ፈተና ገጥሞት ነበር፡፡ ከዚህም ሌላ ከመንገዱ ጎን የተዘረጋው የቴሌ መስመር እና የቴሌ ታወር በፈንጂው ምት የመሬት ንቅናቄ እንዳይወድቅ ተብሎ አሰሪው ወገን ታወሩን አንስቶ ቦታውን ነፃ እስኪያደርግ ድረስ ለ8 ወራት የመጠበቅ ሁኔታ ሁሉ ፕሮጀክቱን አጋጥሞታል፡፡ እነዚህ ሁሉ ተግዳሮቶች ፕሮጀክቱን ቢያጋጥሙትም ሁሉንም በዘዴ በመያዝ እና ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ ችግሮች ተፈተዋል፡፡ በአሁኑ ወቅት የፕሮጀክቱ ሥራ በአብዛኛው ተጠናቆዋል ማለት ይቻላል፡፡

የሐረር ባይ ፓስ የመንገድ ስራ ፕሮጀክት ከዕቅዱ በላይ በመሥራት በበጀት ዓመቱ ውስጥ ቫትን ጨምሮ ብር 174 ሚሊዮን ገደማ አስገብቷል፡፡

## 5.4. Harar-By-Pass Asphalt Road Project

The road project is located in Harar town in Harari National Regional State and Oromia National Regional State in Eastern part of the Ethiopia. It consists of construction of 20KM Asphalt Concrete road.

The project suffered from frequent work interruption and stoppage, which has been the major challenge throughout the project duration, and hence, regularly dealing with the local residents, community clan and local administration has become part of the project's day to day activities. This clearly affected the normal project work progress.

In addition, huge rock excavation encountered in the town section and near public infrastructure i.e. Tele Tower, which totally suspended the work around until the client removes and relocate the infrastructure that took nearly 8-months' time. The unique operation work and methodology of executing on such characteristics of the rock nature was also another challenge that hindered the progress of the work beyond the plan.

Despite the above facts, the Company has made all possible efforts to liaison with the local administrative officials, nearby farmers and the stakeholders to overcome the problem. Along with such challenges, currently the project was substantially completed.

The project financially performed well above the plan (close to Birr 174 million including VAT) during the year.




Figure 6: Plan VS Actual Accomplishment





*Modern Mobile Asphalt Batching Plant*




*Completed Asphalt Section at Harar-By-Pass Road Project*

## 5.5. የኢሊሊ ኢንተርናሽናል ሆቴል ሁለገብ የህንፃ ግንባታ ፕሮጀክት

ገምሹ በየነ ኮንስትራክሽን የኢሊሊ የህንፃ ግንባታ ለመፈፀም እህት ኩባንያ ከሆነው ኢሊሊ ኢንተርናሽናል ሆቴል ጋር ውል የፈረመው በህዳር ወር 2006 ዓ.ም ነው፡፡ የግንባታው ስራ ቁጥጥር ኤም. ጂ. ኤም አማካሪ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር (MGM CONSULT PLC) በሚባል አማካሪ ድርጅት እየተሠራ ይገኛል፡፡ የዚህ ፕሮጀክት ስራ የተጀመረው በህዳር ወር 2006 ዓ.ም መጨረሻ ላይ ነው፡፡ ይህ ፕሮጀክት ቀደም ሲል ድርጅቱ ሲሠራቸው ከነበሩት ሥራዎች ለየት አድርጎ እንዲታይ የሚያደርገው ምክንያት አለው፡፡ ይኸውም ድርጅቱ ከነበረበት የመንገድ ስራ አቅጣጫ ወጣ ብሎ ወደ ህንፃ ግንባታ እንዲገባ መንገድ የከፈተ ፕሮጀክት በመሆኑ ነው፡፡ የህንፃው ዲዛይን በጣም ዘመናዊ ሲሆን 2B+G+22 ፎቆች የሚያጠቃልል ረጅም ህንፃ ሆኖ አቀማመጡ ኢሊሊ ኢንተርናሽናል ሆቴል ፊት ለፊት ነው፡፡

ህንፃው በአዲስ አበባ ውስጥ ስምንት ፎቅ ሁለት ፎቅ ከመሬት በታችን ጨምሮ የመኪና ማቆሚያ ያለውና 300 መኪኖች ማስተናገድ የሚችል የመጀመሪያው ብቸኛ ህንፃ ነው፡፡ ይህ አገልግሎቱ ደግሞ ለኢሊሊ ደንበኞች እና ለሌሎችም ወገኖች ያለምንም ችግር መኪኖቻቸውን እንዲቆሙ መብት ስለሚያስችላቸው ለህዝቡ ያለው ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው፡፡

የሆቴሉ ዲዛይን የተሰራው ኤስ. ኬ. ኤ. ኤስ (SKAS) ኮንሰልቲንግ አርክቴክትስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ሲሆን ግንባታው ያረፈበት የመሬት ስፋት 1,330 ካሬ ሜትር ነው፡፡

ፕሮጀክቱ የበጀት ዓመት ዕቅዱን 100% አሳክቷል፡፡ ከዚህ ቀጥሎ የሠፈረው ግራፍ የፕሮጀክቱን የዓመቱን ዕቅድና ስኬት የሚያሳይ ነው፡፡

## 5.5. Elilly International Hotel Multi-purpose Building Project

Gemshu Beyene Construction PLC has signed contract agreement with Elilly International Hotel a sister company for the construction of Elilly Parking and Multiuse Building Complex on the 4th day of November 2014. The construction supervision is currently undertaken by MGM Consult PLC. The Construction of the Project is started in the late November, 2014.

This Project has been uniquely defined among the projects that the company had experienced previously. In addition, it was set as a spring board and opened an opportunity for the company to meet and realize its goals of entering into the construction of building related projects. The design scheme for the building is ultra-modern that comprises 2B+G+22 stories high rise building, which is located adjacent to Elilly International Hotel.

It is the first building of its kind in the City with eight floors of car parking including two basement floors that can accommodate up to 300 vehicles at a time on the parking spaces and hence, intended to serve customers of Elilly International Hotel in particular and the public in general. It was designed by SKAS Consulting Architects PLC. Its total built up area is about 1,330m2.

The project attained 100 % of its annual plan. The figures below shows the project's Plan Vs Accomplishment until the end of fiscal year.




Figure 7: Actual VS Accomplishment

ህንፃው የሚከተሉ ጥቅሞችን ይሰጣል፡፡

- የመኪና ማቆሚያ
- የስብሰባ አዳራሽ
- አጠቃላይ የሆቴል አገልግሎት
- የሱቆች ማዕከል
- በጣም አዝናኝ የሆኑ የእንግዳ ማረፊያዎች ስላሉት እነዚህን ሁሉ ጥቅሞች የሚሰጥ ባለብዙ ሥራ ህንፃ ነው ፡፡

የግንባታው ሁኔታ በአሁኑ ወቅት እጅግ የተፋጠነ ሲሆን ከተመደበለት ጊዜ በፊት ያልቃል ተብሎ ይገመታል፡፡ የሥራው ደረጃ የማጠቃለያ ሥራዎች /Finishing Work/ የፍክስቸር እና የማስመር ወይም የንጣፍ ስራዎች እየተሠሩ ሲሆን ይኸውም በድጋሚ በ2008 ዓ.ም ከሆቴሉ ጋር የተደረገው ስምምነት አካል ሆኖ እየተሰራ ነው፡፡

በበጀት ዓመቱ የመጨረሻ ሪፖርት መሰረት ፕሮጀክቱ የሚከተሉትን ሥራዎች በኮንትራት ውሉ መሰረት ፈፅሟል፡፡

- የኮንክሪት ሥራዎችን እስከ 21ኛው ፎቅ ድረስ ጨርሷል፡፡
- ከሞላ ጎደል የግንብ ሥራውን ጨርሷል፡፡
- የፕላስተሪንግ ሥራውን ከውስጥም ከውጭም በኩል ጀምሯል፡፡
- የጂፕሰም ሥራን በከፊል ጀምሯል፡፡
- የውሃ እና የኤሌክትሪክ ሥራዎችን ጨምሮ የማጠቃለያ ሥራውን ለመጀመር ዝግጅት ጨርሷል፡፡
- የመኪና ማቆሚያ ወለሎች ለኢሊሊ ኢንተርናሽናል ሆቴል ደንበኞች ጊዜያዊ አገልግሎት መስጠት ጀምረዋል፡፡



*Elilly Multi-purpose Buliding Complex (Side View)*

The building is intended to have the following main functions.

- Car parking
- Considerably big meeting hall
- General hotel services
- Shopping centers, and so forth
- Luxury guest houses,

The current progress of the project is extra ordinary and is expected to be completed ahead of anticipated schedule. Currently the Company is doing finishing works, fixtures, and furnishing based on the supplementary agreement signed with the Hotel in 2015/16 G.C.

During the reporting period, the project has accomplished construction of the following building works as per the agreement.

- Completed all concrete works (structural Part) up to 21st story.
- Substantially completed block works.
- Commenced plastering works (Outside and inside) face.
- Commenced partial Gypsum activities.
- Prepared to Start finishing works including sanitary and electrical works, Etc.

The car parking floors of the building has put in service provisionally for customers of Elilly International Hotel.



*Elilly Multi-purpose Buliding Complex (Front View)*

## 5.6 የአምቦ ከተማ የውስጥ ለውስጥ የአስፋልት መንገድ ሥራ ፕሮጀክት

የአምቦ ከተማ የውስጥ ለውስጥ የአስፋልት መንገድ ሥራ ፕሮጀክት በቅርቡ ከተጀመሩት አዲስ ፕሮጀክቶች አንዱ ሲሆን የኮንትራት ውሉ በድርጅታችን እና በኦሮሚያ ገጠር መንገዶች ባለሥልጣን መካከል የተፈረመው የካቲት 25/2016 ነው፡፡ የፕሮጀክቱ መንገድ ሥራ በአራት ዓመታት ውስጥ ያልቃል ተብሎ ይገመታል፡፡

የመንገዱ ግንባታ የሚያጠቃልለው አዳዲስ መንገዶችን መክፈት፣ የነበረውን መንገድ ደረጃ በማሻሻል በጠጠር ማልበስ እና በከተማ ውስጥ በአስፋልት የመሸፈን ሥራዎችን ነው፡፡ ፕሮጀክቱ በ6 /ስድስት/ ቦታ የተከፋፈለ ሆኖ በአጠቃላይ 15 ኪ.ሜትር ርዝመት ያለው እና የመንገዱ ስፋት ከ18 ሜትር 30.5 ሜትር የሚደርስ ነው፡፡

ይህ የአምቦ የመንገድ ሥራ ፕሮጀክት ሲጠናቀቅ አሁን በከተማዋ ውስጥ ያለውን የተጨናነቀ የትራፊክ ችግር የሚያቃልል እና ከተማዋ አዳዲስ አማራጭ መንገዶች እንዲኖራት በማድረግ የህብረተሰቡን ችግር ይቀርፋል ተብሎ ይጠበቃል፡፡

ይህንኑ ሥራ ለማቀላጠፍ ድርጅታችን የኮንትራት ውሉን እንደተፈረመ ዋናውን ሥራ ሊያስጀምሩት የሚችሉትን ቅድመ ዝግጅቶች ወዲያውኑ ጀምሮ ሥራ ላይ አውሎአል፡፡

በዚሁም መሠረት፡-

- ሁሉም የሰርቬይንግ ሥራ ማለትም የኮንትሮል ነጥቦች ምሥረታ፣ የትራቨርስ ሥራ፣ የሌቨል ሥራዎች ፣ የክሮስ ሴክሽን ሥራዎች እና የቶፐ ንባቦች ሥራ ዝግጅት፣
- የዲዛይን ግምገማ የቴምፐሌት ዝግጅት ሥራ፣
- የወሰን ማስከበር ቦታዎችን የመለየት እና ለሚመለከተው አካል ጥያቄ የማቅረብ ሥራ ፣
- የተለያዩ የድንጋይ እና የማቴሪያል ማምረቻ ቦታዎች የማሰስ እና የአስፈቅዶ የመያዝ ሥራ፣
- የካምፐ ቦታን የመለየት እና ተረክቦ ግንባታ የመጀመር ሥራ፣
- የድንጋይ ምርት ሥራ ፣
- ክሬሸር የማጓጓዝ እና የመትከል ሥራ፣
- የጠጠር መፍጫት ሥራን የመጀመር ሥራዎችን አከናውኗል፡፡

ዋነኛው እና ቋሚው የፕሮጀክቱ ሥራ በመጪው ዓመት የሚጀመር ሲሆን በኮንትራት ውሉ መሠረት ዋና እንቅፋት ይሆናሉ ተብለው ከሚታሰቡት ውስጥ የወሰን ማስከበር ስራዎች በሚገባ መፈፀም እንደሚኖርባቸው ይታመናል፡፡ ምክንያቱም በመንገዶቹ ዙሪያ በጣም ብዙ ህዝብ የሚኖር ከመሆኑ አኳያ የወሰን ማስከበሩ ሥራ ከወዲሁ ካልተጠናቀቀ በፕሮጀክቱ ሥራ ላይ ተግዳሮት ሊሆን ስለሚችል ሊታሰብበት የሚገባ ነው፡፡

## 5.6. Ambo Town Asphalt Road Project

Ambo Town Asphalt road project was among the newly introduced road projects that was recently signed between the Company and Oromia Roads Authority (ORA) in 25th February 2016. The road project was expected to be completed within four years calendar days. The construction work consists of construction of new and upgrading existing gravel to asphalt concrete road within the city. The project has been categorized to 6 (six ) segments adding to the total of 15km length with the width of the road prism ranging between 18m-30.50m.

The road project expected to improve the current traffic management of the city by providing alternative access to other parts of the city roads for the community and public.

Soon after signing of the contract agreement the company has quickly started all the preparatory works that will enable to commence the permanent works.

Among this, the company has performed the following basic activities as to establish the required preparatory works for the upcoming permanent works:-

- All surveying works that was not limited to (Control Points Establishment, Traverse Running, Differential level running and cross section topo readings),
- Design review and working template preparations,
- ROW obstruction identification and request for removal,
- Different quarry site material investigation and possession,
- Camp site identification, possession and construction,
- Quarry material Production,
- Crusher Mobilization and installation
- Commencing crushing activities.etc

Critical permanent project activities will be fully commenced next year provided that obstruction removal is completed in line with the contract agreement and the company plan, which is expected to be the major challenge of the project as there are many residents leaving by and on the side of the road.

## 5.7 አርሲ ዩኒቨርሲቲ የህንፃ ግንባታ

ገምሹ በየነ ኮንስትራክሽን ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ክልል ውስጥ የሚሠራውን የአርሲ ዩኒቨርሲቲ ህንፃ በአርሲ አሰላ ከተማ ውስጥ ለመገንባት ከአርሲ ዩኒቨርሲቲ ጋር በፈረንጆቹ አቆጣጠር ሚያዝያ 11/2016 የኮንትራት ውል ፈርሟል፡፡ የዚህ ፕሮጀክት ሥራ በ700 የሥራ ቀናት ውስጥ ይጠናቀቃል ተብሎ ይጠበቃል፡፡



*Construction While in Progress/Arsi University*

የአርሲ ዩኒቨርስቲ የህንፃ ግንባታ ድርጅቱ በታሪኩ ውስጥ ለሶስተኛ ወገን ህንፃ ለመገንባት ሲዋዋል የመጀመሪያው ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

በአሁኑ ወቅት በፕሮጀክቱ ላይ የቋሚው ሥራ አካል የሆኑ የጠረጋ / Clearing/ ሥራ የመሠረት ቁፋሮ ሥራዎች ያበቁ ሲሆን የስትራክቸር ዋነኛ ሥራዎች የሆኑት መሠረት የማንጠፍና የካስቲንግ ሥራዎች ተጀምረዋል፡፡

## 5.7. Arsi University Building Project

Gemshu Beyene Construction PLC has signed a contract agreement with Arsi University located in Oromia National Regional state for the construction work of parts of University building project to be constructed in Arsi Assella. The project is expected to be completed within 700 calendar days as per the contract agreement signed on 21st April 2016.



Arsi University building project contract signing was considered to be the first in the history of the company for constructing building projects for third party.

Currently, the permanent activities that include site clearing, bulk excavation and foundation excavation were completed and the main structural works of foundation footing casting started.

ሰባት ጉጂ ነገሮች

- **ሥራ ያልታከለበት ሀብት**
- **እምነት የሌለበት ደስታ**
- **ፀባይ አልባ ዕውቀት**
- **መስዋዕትነት የሌለበት ሃይማኖት**
- **መመሪያ የሌለው ፖለቲካ**
- **ስብእና የሌለው ሳይንስ**
- **ስነ-ምግባር የሌለበት የንግድ ሥራ**

ማሃተማ ጋንዲ

There are seven things that will destroy us:

- **Wealth without work;**
- **Pleasure without conscience;**
- **Knowledge without character;**
- **Religion without sacrifice;**
- **Politics without principle;**
- **Science without humanity;**
- **Business without ethics.**

Gandhi (1869-1948)

# 6 ዓመታዊ የጠቅላላ ሠራተኞች ስብሰባ
## Annual Staff Assembly Meeting

ገምሹ በየነ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ኩባንያ ተጋባዥ እንግዶችና የኩባንያው የሥራ አጋሮች በተገኙበት ዓመታዊውን የጠቅላላ የሠራተኞች ጉባኤ ጷጉሜ 6 ፣ 2007 ዓ.ም በኢሊሊ ኢንተርናሽናል ሆቴል በደማቅ ሁኔታ አካሂዷል፡፡

በወቅቱም የኩባንያው ዓመታዊ የሥራ እንቅስቃሴ ሪፖርት በከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች ቡድን አባላት ቀርቧል፡፡ በዓመቱ የኩባንያው ዋና ዋና ስኬቶች እና ባጋጠሙ ተግዳሮቶች እንዲሁም ችግሮች ዙሪያ ውይይት ተካሒዶ በከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች የተቀመጠውን ቅድመ ግምት በማካተት የ2008 ዓ.ም የሥራ ዘመን ዕቅድ ተዳሷል፡፡

በዝህ ዓመታዊ የጠቅላላ ሠራተኞች ጉባኤ ላይ 25 የላቀ የሥራ አፈጻጸም ላስመዘገቡ የምሥክር ወረቀት እና ቦነስ ሲሰጥ ለአስራ ሰባት ሰራተኞችም እንዲሁ የእውቅና ምሥክር ወረቀት ተሰጥቷል፡፡ የዕለቱ ልዩ ሽልማት ደግሞ የግሬደር ኦፕሬተር ለሆኑት ለቀድሞ የኩባንያው ሠራተኛ ለአቶ ጉተማ ገመቹ ተበርክቷል፡፡ ዲማ - ፍየል ውሃ አስፋልት መንገድ ፕሮጀክት ከኮንትራት ጊዜው አስቀድሞ በመጠናቀቁ እንዲሁም በመሃልሜዳ - ዓለም ከተማ አስፋልት መንገድ ፕሮጀክት ለISO 9001፡2008 መመሪያ መተግበር ለታየው ቁርጠኛ አፈጻጸም የዋንጫ ሽልማት ተበርክቷል፡፡

በዕለቱም በሙያ ሥነ-ምግባር እና ዲሲፕሊን ዙሪያ ያተኮረ የሠራተኛውን ተነሳሽነት እንዲሁም ትጋት የበለጠ ለማሳደግና ግንዛቤ ለማስፋት ያለመ የማነቃቂያ ሥልጠና ከራይት ቪዥን ኢንተርናሽናል ኃ/የተ/የግል ኩባንያ በመጡት ወ/ሮ ሙሉ ሰለሞን ተሰጥቷል፡፡





*Partial View of Annual Assembly*

Gemshu Beyene Construction (GEBECON) PLC has colorfully held its annual assembly of staff members on September 06, 2015 at Elilly International Hotel in the presence of invited guests and company business partners.

On the occasion, a report on company annual performance was presented by the top management team members. A discussion was held on the major achievements, challenges and problems facing the company including briefings on 2008 E.C fiscal year plan and the expectation set out by the top management.

The event was concluded by handing out awards in the form of certificate and bonus to 25 best performing employees. A certificate of recognition was also given to seventeen employees. A special award went to the late staff member, Ato Gutama Gemechu, Grader Operator. Moreover, a trophy award was also presented to Dima-Fiyel Wuha Asphalt Road Project for completing the project head of the contract period, and Mehal Meda Alem-Ketema Asphalt Road Project for adherence to and successful implementation of ISO 9001:2008.

On the occasion, refreshment training on work etiquette or discipline was organized and conducted in order to further develop staff commitment and raise their awareness in the subject area. The training was facilitated by W/o Mulu Solomon of RIGHT VISION INT.PLC.










*Partial View of Awards Cermony*

# 7 የገበኮን ፕሮጀክቶች ዕቅድና አፈጻጸም ግምገማ
# Project Plan and Progress Review Meeting

የገበኮን ከፍተኛ የሥራ አመራር ግንቦት 10 ፤ 2008 ዓ.ም በኢሊሊ ኢንተርናሽናል ሆቴል ዓመታዊውን የፕሮጀክት አፈጻጸም ግምገማ ስብሰባ አካሂዷል፡፡

ስብሰባው በኩባንያው ዋና ሥራ አስኪያጅ በአቶ ገምሹ በየነ ንግግር የተከፈተ ሲሆን በንግግራቸውም የስብሰባው አስፈላጊነት የኩባንያውን ዓመታዊ ዕቅድ አፈጻጸም ለመገምገምና ለመመዘን በማስቻል ተጠያቂነትን በመፍጠር በሁሉም ደረጃ ውጤታማ በመሆን ለመሻሻል ዕድል ይፈጥራል ሲሉ አጽንኦት ሰጥተው ተናግረዋል፡፡

የዋና ሥራ አስኪያጁን ንግግር ተከትሎ የኩባንያው የ2008 ዓ.ም የፕሮጀክቶች አፈጻጸም ምዘናና ግምገማ የተካሔደ ሲሆን የእያንዳንዱ ፕሮጀክት ሥራ አስኪያጆች ባለፉት የዘጠኝ ወራት አፈጻጸም ወቅት የተገኙ ስኬቶች ፣ ቁልፍ ተግዳሮቶችና ችግሮች ላይ የከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎችን ትኩረት የሚሹትን በመለየት ሪፖርት አቅርበዋል፡፡ በሪፖርቶቹ ይዘት ላይ ጥልቅ ውይይት ከተካሔደ በኋላ የትኩረት አቅጣጫ በሚሹትና በፕሮጀክት ሥራ አሥኪያጆች እንዲሁም በሚመለከተው የዋና መሥሪያ ቤት አካል በኩል መቀረፍ ባለባቸው ጉዳዮች ላይ በከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች አቅጣጫ ተሰጥቷል፡፡

The top management of GEBECON PLC has held its annual project performance review meeting on May 02, 2016 at Ellily International Hotel.

The meeting begun with the opening remark made by the General Manager, Mr. Gemshu Beyene. The General Manager stressed the significance of the meeting, which helps to review and evaluate the annual plan performance of the company in order to provide opportunities for further improvement and uphold accountability and compliance at all levels.

Following the opening remark, the meeting focused on the review and evaluation of the company's projects performance for the 2015/16 fiscal year. During the review meeting, the respective project managers have presented a detailed nine months performance report including the accomplishments made, key challenges and problem areas, which require the utmost attention of the top management. After thorough discussion on the contents of the report, directions were given by top management on major issues of concern, which needs to be addressed by both the respective projects and the H.O organs.



*Partial View of Review Meeting*

# 8 የገበኮን አምስት ዓመት ስትራቴጂ ዕቅድ ዝግጅት ምዘና ወርክሾፕ
## Five Years Strategic Plan Development Revalidation Workshop

የገበኮን ኃ/የተ/የግል ኩባንያ ከፍተኛ የሥራ አመራር ግንቦት ፲፩ ፣ 2008 ዓ.ም በኢሊሊ ኢንተርናሽናል ሆቴል የኩባንያውን የአምስት ዓመታት የስትራቴጂ ዕቅድ ዝግጅት ምዘና ወርክ ሾፕ አካሂዷል፡፡

ዋና ሥራ አስኪያጁ ወርክ ሾፑን ሲከፍቱ በኮንስትራክሽን ዘርፍ የኩባንያውን ወቅታዊ ይዞታ በማጠናከር ብሎም የተወዳዳሪነት ብልጫውን በማስቀጠል ረገድ የአምስት ዓመቱን ስትራቴጂ ዕቅድ መመሪያ ተግባራዊ ማድረግ ያለውን የላቀ ጠቀሜታ አጽንኦት ሰጥተውበታል፡፡

የኩባንያውን ስትራቴጂ መመሪያ ዋልታዎች (strategic pillars) አቅጣጫ ለማስያዝ በሚል የቀረበውን ውስጣዊና ውጫዊ የሥራ ሥነ-ምህዳር ትንተና ውጤት ለመመዘን ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች ሰፋ ያለ ውይይት ካካሔዱ በኋላ የስትራቴጂ ዕቅድ ዝግጅት ሒደቱን ደግፈው መሰረታዊ የስትራቴጂ አስተሳሰቦች ጋር ለማስተሳሰር ገንቢ ሐሳቦችንና ግብአቶችን አቅርበዋል፡፡

በመጨረሻም የተሰጡ ሀሳቦችን በማካተት የዕቅድ ዝግጅቱ በአፋጣኝ ተጠናቆ በመጪው የሥራ ዘመን ወደ ተግባር እንዲገባ በሚል ሥራ አመራሩ በጋራ ስምምነት ላይ ደርሷል፡፡

The top management of GEBECON PLC has held a one day revalidation workshop on five years strategic plan development on May 03, 2016 at Ellily International Hotel.

During the opening of the workshop, the importance of developing and putting into effect a five year strategic plan so as to strengthen the position of the company and maintain its competitive advantage within the construction sector was emphasized by the General Manager.

An extensive discussion was held by the top management in order to revalidate the results of the internal and external environmental analysis so as to redefine the company's strategic pillars. Valid inputs were provided by the top management to the assumptions and presumptions underpinning the strategy development process during the workshop.

Finally, the management reached at unanimous agreement to incorporate the comments and finalize the development of the plan as soon as possible in order to start its implementation as of the next fiscal year.



*Partial View of Revalidation Workshop*

# 9 የሰው ኃይል ልማትና ሥልጠና ሥራዎች እንቅስቃሴ
## Staff Training and Development Activities

የኩባንያው የውስጥ አቅም ግንባታ ፕሮግራም አካል የሆኑ በርከት ያሉ የተለያዩ የአጭር ጊዜ የሥልጠና ፕሮግራሞች በየዓመቱ ተዘጋጅተው ለከፍተኛ የማኔጅመንት አባላትና ሠራተኞች ይሰጣሉ፡፡ የነዚህ ሥልጠናዎች ዋና ዓላማ የሠራተኞችን አመለካከት ፣ እውቀት እንዲሁም ክህሎት ወይም ባህሪ በመማማር ሒደት ውስጥ ከፍ ወዳለ ደረጃ በማምጣት ምርታማነታቸውንና የመፈጸም ብቃትን ለማሻሻል ያለሙ ናቸው፡፡

ሰኔ 2008 ዓ.ም በተጠናቀቀው የሥራ ዘመን ኩባንያው የተለያዩ ሥልጠናዎችን አካሒዷል፡፡

ከነዚህም ሥልጠናዎች ከጷጉሜ 4 እስከ 5 ቀን 2007 ዓ.ም በኢሊሊ ኢንተርናሽናል ሆቴል የተካሔደው 36 ከፍተኛና መካከለኛ የሥራ አመራር አባላት የተሳተፉበት በግል ለውጥና ዕድገት ላይ ያተኮረው ሥልጠና ተጠቃሽ ነው፡፡ የዚህ ሥልጠና ዓላማ የሥራ አመራር አባላቱን ግላዊ ባህሪ በማበልፀግ ድርጅቱንና ሰዎችን በመምራት ሒደት ውስጥ አመቺ የሆነ የሥራ ከባቢን ለመፍጠር ያለመ ነው፡፡ ሥልጠናው በቀድሞዋ የንግድ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት እና የራይት ቪዥን ኢንተርናሽናል ኃ/የተ/የግል ኩባንያ ዋና ሥራ አስኪያጅ በሆኑት በወ/ሮ ሙሉ ሰለሞን ተሰጥቷል፡፡

በተመሳሳይ መልኩ በዋናው መሥሪያ ቤት እንዲሁም በማዕከላዊው ጋራጅ እና በተለያዩ የፕሮጀክት መስኮች ለሚሰሩ 34 መካኒኮች እና ቴክኒሻኖች የSIS(Service Information System) የሁለት ቀናት ሥልጠና ተሰጥቷል። የንድፈ ሀሳብ እና ተግባራዊ (diagnosis and trouble shooting and using ET-Electronics) ሂደቶችን ያካተተው ሥልጠናው ከሪዬስ ኢንጂነሪንግ (RIES ENGINEERING) በመጡ ባለሙያዎች የተካሔደ ነበር፡፡

በተለያዩ ማሽኖች ላይ ለሚሰሩ ኦፕሬተሮች ከጷጉሜ 4 እስከ 5 ቀን 2007 ዓ.ም በሪዬስ ኢንጂነሪንግ (RIES ENGINEERING) የተሰጠው ጠቅላላ የጥገና ፣ ውጤታማ ኦፕሬሽን እና የመሳሪያ አጠቃቀም ሥልጠና (general service, effective and efficient operating system, and equipment handling method) እንዲሁ የኦፕሬተሮችን ውጤታማነት ለማሳደግ ያለመ ነበር፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ለ30 ቴክኒሻኖች ፣ መካኒኮች እና ለከባድ ጭነት አሽከርካሪዎች በጥገና ፣ እድሳት እንዲሁም በሥራ ላይ የሚያጋጥም እክሎችን በመከላከል (maintenances, service, and possible down protections) ዙሪያ ከኒያላ ሞተርስ (NIYALA MOTORS) በመጡ ባለሙያዎች ለሁለት ቀናት ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡

ገበኮን ከግንቦት 13 እስከ 16 ፣ 2008 ዓ.ም በኢሊሊ ኢንተርናሽናል ሆቴል በዋናው መሥሪያ ቤት እና በፕሮጀክቶች መስኮች ለሚሰሩ 12 የውስጥ ኦዲት ቡድን አባላት በISO 9001:2008 ሥርዓት ዙሪያ ሥልጠና ሰጥቷል፡፡ ሥልጠናውም በዋነኛነት የውሥጥ ኦዲት ጠቅላላ አሰራር እና መሰረታዊ ጽንሰ ሃሳቦች ላይ በማተኮር በተጠናቀቀው ዓመት ስኬታማ ሆኖ እንደተፈጸመው ሁሉ የተሻለ ዓመታዊ የስስተም መፈተሻ ስልት ለመፍጠር ያለመ ነበር፡፡

Each year the company organizes and conducts various short term training programs for its employees and top management members. The main objective is to improve employees' productivity and performance through learning process geared to upgrade their attitude, knowledge, skill or behavior.

For the fiscal year just ended June 2016, the Company organized and conducted different short terms trainings on different topics.

One of such training was on personal change and development, in which 36 top and middle management members have taken part at Elilly international Hotel from September 4- 5/2015. The objective of the training was to help the management members to advance their personality in leading organization and people through creating conducive work environment. The training was facilitated by Right Vision International PLC General Manager W/ro Mulu Solomon (the ex -president of chamber of commerce).



*Partial View of Top Management Training*

Similarly, two days short term training was organized for 34 mechanics and technicians working at head office, central garage and at different project sites on SIS-Service information system. The training consists of both theoretical foundation and practical exposure on diagnosis and trouble shooting and using ET-Electronics. The training was facilitated by trainers from RIES ENGINEERING.



በተጨማሪም 13 የሒሳብ ባለሙያዎች (accountants) በሒሳብ አያያዝ ዘዴ (accounting system) ሥልጠና ሲወስዱ 16 የግዢ ባለሙያዎችም (purchasers) በሎጂስቲክ አስተዳደር ፣ የግዢ ሥራዎች እና የአቅርቦት አስተዳደር ዘዴዎች ዙሪያ በኢሊሊ ኢንተርናሽናል ሆቴል የተዘጋጀውን የሁለት ቀናት ሥልጠና ወስደዋል፡፡

ከዚህም ባሻገር በዓመቱ በተደረገው የሠራተኞች ጉባኤ ወቅት እንዲሁ ከአዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ ጋር በመተባበር በተለያዩ የፕሮጀክት ቦታዎች ለ414 ሠራተኞች በሥራ ቦታ ደህንነት፣ አጠባበቅ ፣ በአደጋ መከላከል ፤ የሙያ እና የሥራ ቦታ ሥነ-ምግባር ላይ የማነቃቂያ ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡

የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች በተለያዩ የመስክ ፕሮጀክቶች ላይ በመሳተፍ ተግባራዊ ልምምድ እንዲቀስሙ በማስቻል ኩባንያው ለዩኒቨርሲቲ እና ኢንደስትሪ ትስስር ፕሮግራም የጎላ አስተዋፅኦ እያበረከተ ይገኛል። በዚህ ዓመት ብቻ 42 ተማሪዎች በኩባንያው ውስጥ የነበራቸውን የተግባር ልምምድ ወይም ኢንተርንሺፕ ፕሮግራም በስኬት አጠናቀዋል። በኩባንያው የኢንተርንሺፕ ፖሊሲ መሠረትም በተለያዩ የመስክ ፕሮጀክቶች ተግባራዊ ዕውቀት እንዲቀስሙ ለማስቻል የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን መቀበሉን ይቀጥላል፡፡



*Partial View of Accountants Training*



*Congradulatory Message from Client Rep.(AIC)*



*Partial View of Operators & Technicians Training*

The other training given for operators working on different machineries by RIES ENGINEERING from September 4-5/2015 was on general service, effective and efficient operating system, and equipment handling method, which was destined to increase the output of operators in the field. Moreover, trainers from NIYALA MOTORS facilitated two days training on the maintenances, service, and possible down protections for 30 technicians, mechanics and drivers of Dump trucks.

GEBECON PLC also organized training on ISO 9001:2008 at Elilly International hotel from April 21-24, 2016 for 12 internal audit team members working at H.O and project sites. The training delivery was focused on the general framework and basic principles of internal audit function in order to facilitate better system application check up annually, which was successfully accomplished during the reporting period.

Additionally, 13 accountants took training on accounting system while 16 purchasers have attended training on logistic management, purchase activities and supply management system for two days at Elilly international hotel.

Furthermore, 414 employees took refreshment training on workplace safety and accident management including etiquette and workplace discipline. The training was organized and facilitated during annual staff assembly meeting and at different project sites in collaboration with Awash Insurance Share Company.

The company is also making major contribution to university and industry linkage program by providing university students the opportunity for practical attachment at its different project sites. This year alone, 42 students have successfully completed their internship program at the company. As part of its internship policy, the company will continue accepting university students for practical training at its different project sites.

# 10 የኮንስትራክሽን ፕላኒግ እና ኮንትራት አስተዳደር እንቅስቃሴዎች
# Construction Planning and Contract Administration Activities



**አስፋው ዲሪብሳ**
የእቅድ እና የኮንትራት አስተዳደር ሃላፊ
**Asfaw Diribssa**
Manager, Construction Planning and Contract Administration Dep't

ተወዳዳሪዎች በበዙበት እና ዘርፈ ብዙ በሆነው የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ውስጥ ስንጓዝና የግንባታ ውል በምንዋዋልበት ወቅት የሥራ ዓይነትና መጠን ለሥራው የተመደበ ጊዜ እንድሁም ኃለፊነቶችና ግዴታዎች በሚገባ ማወቅና ጥንቃቄ ማድረግ ወሳኝ ሥራ መሆኑ ይታወቃል፡፡

ከኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ለውጥ ጋር ለመሄድ ገምሹ በየነ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማ. ካደረጋቸው ውሣኔዎች አንዱ የኮንስትራክሽን ፕላኒንግ እና ኮንትራት አስተዳደር ዲፓርትመንት ለብቻው በማቋቋም የፕላኒንግ እና ኮንትራት አስተዳደር እንዲመራ ማድረጉ ነው፡፡

የኮንስትራክሽን ፕላኒንግና አስተዳደር የሥራ ሂደት በብስለት እና በብቃት መከታተልና የኮንስትራክሽን ውሉን በመመሥረት የሥራ አፋፃፀሙ በተገባው ውል መሠረት በመተግግበር ሥራ አፈፃፀሙ ከፍ እንዲል እና ኪሣራ እንዲቀንስ በሚገባ መከታተልና ትንታኔ እየሰጡበት ማስፈፀም ነው፡፡

ሥራውን በጥልቀት በመረዳት እና በመምራት የፕሮጀክቱን የሥራ ጊዜ የሥራ ጥራት ወጪውን እና ገቢውን መቆጣጠር የኮንስትክሽን ፕላንግ እና ኮንትራት አስተዳደር መምሪያው ዋና ተግባር ነው፡፡

ከዋና ዋና ሥራዎቹ ውስጥ፡-

- የጨረታ ሰነድ ማዘጋጀት፣ በኮንትራት ውሉ ሰነዶች ላይ ከደንበኛው ጋር ተወያይቶ በመግባባት ከፍፃሜ ማድረስ፤
- ኮንስትራክሽን ዕቅዱን እና የፕሮጀክቶች የሥራ ፕሮግራም ማዋሃድና ማዳበር
- ክሌም(ስሞታ) የሚቀርብባቸውን ሥራዎች ለይቶ በማውጣት ሁሉም የኮንትራት ባለድርሻዎች እንዲያውቁት እና እንዲከታተሉት በማድረግ ኪሳራን መቀነስ፤

Today's competitive and complex construction industry requires careful consideration in the formation of the construction contract to ensure that the specifications and timetable are feasible and risks and obligations are clearly defined in a contract agreement. Among the actions taken to move along with dynamics of the Construction Industry, Gemshu Beyene Construction PLC has established Construction Planning and Contract Administration at Department level to manage planning and contract administration of the company.

Construction planning and contract administration is the process of systematically and efficiently managing Contract formation, execution and analysis for maximizing operational and financial performance and minimizing risks. Understanding and establishing a management system that control Time, Quality and Cost of a project are vital tasks of Construction Planning and Contract Administration Department.

The main tasks of the Department are:

- Preparation of bid, negotiating appropriate contract terms and conditions with the Clients
- Construction Planning and Scheduling of projects and updating of the same
- Indentify potential claim and making aware all stake holders of the contract potential claims and procedures to follow in order to minimize same.

- የድርጅቱን እና ፕሮጀክቶችን የኮንትራት ጉዳይ ማስተዳደር፤
- የፕሮጀክቶችን ሳምንታዊ፣ ወርሓዊ እና ዓመታዊ የሥራ አፈፃፀም መገምገም፤
- የፕሮጀክቶችን የጊዜ፣ ጥራትና የዋጋ ሁኔታ እና ያለውን ተጽእኖ መከታተል፤
- የካምፓኒውን እና የፕሮጀክቶችን የዶክመንቶች አያያዝ መምራት፤

የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪን ውስብስብ ባህርይ በመረዳት እና ኮንትራቱን በማወቅ ድርጅቱ ቀደም ሲል በነበረው ጠንካራ ጉዞ ላይ የራሱን ሚና በመጫወት መምሪያው በፕሮጀክቶች የሥራ ስኬት ላይ ተጨማሪ ውጤት አስገኝቷል፡፡

ገበኮን በከፍተኛ ጥረት እና በተያዘለት ጊዜ የኮንስትራክሽን ሥራውን እየፈፀመ ለአሰሪው ማስረከቡን እንዲቀጥልበት የፕላንንግና ኮንትራት አስተዳደር መምሪያ ምን ጊዜም ያላሰለሰ ጥረት ማድረጉን ይቀጥላል፡፡ መምሪያው አዳዲስ ሓሳቦችን እያፈለቀ እና ተግባራዊ እያደረገ ድርጅቱ በኢንጂነሪንግ በኩል አሁን ካለው በላይ ጠንካራ ሆኖ እንዲወጣ ያልተቆጠበ ጥረቱን ያደርጋል፡፡

- Contract Management of projects and the company
- Carry out Weekly , Monthly and Annual Progress Evaluation of projects
- Follow up of projects with issues having time, quality and cost effects on projects, and
- Manage proper Documentation of Projects and company.

With understanding of complex nature of construction industry and associated contract, the Department has played its role and added values in the already established good reputation of the Company's performance in terms of project accomplishment.

To make sure that GEBECON remains strong in the provision of highest quality and timely construction works to its clients, the Planning and Contract Administration Department relentlessly work in building stronger capacity to meet the rising demand in the years to come. The Department further, by implementing innovative ideas and customizing best practices, will make every effort to enable the Company excel in most aspect of engineering practices.

**"በየቀኑ ጠዋት ጠዋት የውሎህን ዕቅድ ለማውጣት አሥራ አምስት ደቂቃ ብታጠፋ ምርታማነትህ በሃያ % /መቶኛ / ይጨምራል።"**

አኖኒሞስ

**"If you spend fifteen minutes planning your day on paper every morning, you will add 20 percent to your productivity."**

Anonymous

# 11 ወደፊት አርቆ መመልከት - የስትራቴጂ ዕቅድ ዝግጅት
# Looking Ahead - Strategic Plan Development



**ዶ/ር ፋንታ ተስገራ**
የኩባንያው አማካሪ
**Dr. Fanta Tesgera**
Company Adviser

ዛሬ በተቋማት ውስጥ የሚገኝ ስኬት ለነገ ዋስትና ሊሆን አይችልም፡፡ የድርጅቶች ትልቁ መመዘኛ ወደፊት በተከታታይ ሊመጣ የሚችለውን አስቀድሞ መመልከት መቻል ነው፡፡ ለዚህም ነው የስትራቴጂ አስተሳሰብ የድርጅቶች የረዥም አመታት መገለጫ ባህሪ ተደርጎ የሚወሰደው። ፈጣንና የላቀ መሻሻል እያሳየ ባለው የወቅቱ የሉዓላዊነት ወይም ግሎባላይዜሽን አካሔድ ውስጥ የስትራቴጂአዊ አስተሳሰብ አስፈላጊነት ከምን ጊዜውም በላቀ ሁኔታ በማደግ ላይ ይገኛል፡፡ ተከታታይና ቀጣይነት ያለው የስትራቴጂ አስተሳሰብ ቀዳሚ እድሎችን ለመጠቀም በሚደረግ ጥረት ውስጥ እንዲሁ የአብዛኞቹ ድርጅቶች መደበኛ ተግባር ሆኖ እየጎላ መጥቷል፡፡

በእርግጥ የዚህ ጽሁፍ መሰረታዊ አላማ የስትራቴጂ መመሪያ እና የስትራቴጂአዊ አስተሳሰብ እድገትን ምንነት ለማሳወቅ ያለመ ባይሆንም ቅሉ በስትራቴጂ ዝግጅት ሒደት የሚስተዋሉ ግራ መጋባቶችንና ግድፈቶችን ለመጠቆም ከግል ተሞክሮዎቼ ጋር የተለያዩ የስትራቴጂ አመራር ጥናቶችን በማስደገፍ በስትራቴጂ አዘገጃጀት ሒደት ዙሪያ የጠራ ግንዛቤ ለመፍጠር ያለመ ነው፡፡ እንዲሑም ገብኮን የነደፈው የአምስት አመት ስትራቴጂ ዕቅድ አላማን ለማስቃኘት ነው፡፡

“ስትራቴጂ በጉባኤ (በክብ) ጠረጴዛ ዙሪያ ቁጭ ተብሎ በይድረስ ይድረስ እንዲሁ በግርድፉ የሚሰካካ ነገር አይደለም፡፡” ይላል ቴሪ ሐለር፡፡

**“ሌላ ሰው ለመሆን መፈለግ ማንነትህን የማጥፊያ መንገድ ነው።”**
ከርት ኮቤይን

**“Wanting to be someone else is a waste of who you are.”**
Kurt Cobain

In organizations, success achieved today does not guarantee success tomorrow. The greatest providence in organizations is thus to continuously have forethought for what comes. That is why strategic thinking has been the defining characteristics of organizations for many years. In the face of globalization, which has gained considerable momentum in its pace and progress, the need for strategic thinking is even on the rise. Perpetual strategic thinking has increasingly been becoming a common practice in most organizations in order to take the first mover advantage.

The purpose of this piece of writing is not to provide an account of how the field of strategy has been developed or how thinking in strategy has been evolved. Rather, it is to briefly highlight on the confusions and the loop holes in the strategy making process by recounting on my personal experience and the discourse in the strategic management literature. It is also to give a bird's eye view on the rationale and objective of developing five years strategic plan at GEBECON PLC.

"Strategy isn't something you can nail together in slapdash fashion by sitting around a conference table." Terry Haller

Strategic thinking is growing in importance as a means to look ahead or to take a long term view of a possible future. The old saying "If you do not know where you are going, then any road will lead you there!" accentuates with the importance of strategic thinking in directing the future intentions and actions

ስትራቴጂአዊ አስተሳሰብ አስቀድሞ ለመገመት ብሎም ወደፊት ሊከሰት የሚችለውን አሻግሮ ለመመለከት አስፈላጊነቱ እያደገ የመጣ ሁነኛ ስልት ነው፡፡ “ወዴት እንደምትሔድ ካላወክ የትኛውም መንገድ ወደ አንድ ቦታ ይመረሃል!” የሚለው ቆየት ያለ አባባል እንደሚያሳየው የስትራቴጂ አስተሳሰብ የአንድን ድርጅት የወደፊት ራዕይና ፍላጎት አቅጣጫ በመቀየስ ረገድ የላቀ ጠቀሜታ እንዳለው ያሳያል፡፡ የስትራቴጂአዊ አስተሳሰብ ውጤት የሆነው የስትራቴጂ ዕቅድ አዘገጃጀት የምንሠራቸውን ስራዎቻችንን በዝርዝር እንድናስቀምጥና እንዴት አድርገን ወደ ግባችን እንደምንደርስ የሚያሳየን መሳሪያ ነው፡፡

በዚህም መሰረት የስትራቴጂ ዕቅድ አዘገጃጀት ስርአት ሒደት የተለየ ጠቀሜታ አለው፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት ለወደፊት በግልፅ የሚፈፀመውን ሂደት የሚያሳየውን ወሳኝ የሆነ እና የጠራ ስትራቴጂያዊ ዕቅድ ከሌለ ስትራቴጂ ለድርጅታዊ ዕድገት እምንት አስተዋፅኦ ስለማይኖረው ነው፡፡ በአንድ ድርጅት ውስጥ ምን ለውጥ እንደመጣ፣ ምን ለውጥ እየተካሄደ እንደሆነ እና ምን ለውጥ መምጣት እንዳለበት በትክክል ለይቶ ለማስቀመጥ ስትራቴጂያዊ አስተሳሰብ በእውነታ፣ በስልት እና በአዎንታዊ አሰራር የተደገፈ ወይም የተሞላ መሆን ይኖርበታል። ያልተመጣጠነ ለውጥ በሚታይበትና እርግጠኝነት በሌለበት ዘመን የወደፊቱም ሰክኖ በማይቀመጥበት ሁኔታ ስትራቴጂአዊ እውቀት መፍጠር (መጠቀም) እና አማራጮችን ማመንጨት እና የተሻለ የተወዳዳሪነት እድሎችን መፍጠር አይነተኛ አካሔድ ነው፡፡

**“ሌሎችን የሚያምን ሰው ሰዎችን ከማያምን ያነሰ ስህተት ይፈፅማል።”**

ካቩር

**“The man who trusts other men will make fewer mistakes than he who distrusts them.”**

Cavour

በተለይ በምድራችን የቴክኖሎጂ ምህዳር እጅግ እያየለ የመጣው የለውጥና የሽግግር ሒደት የሰብዐዊ ፍጡራንን ህይወት ብቻ ሳይሆን እየለወጠ ያለው ይልቁንም በተለምዶ የነበረውን የንግዱ የአሰራር አካሔድ ሃይሉን ከንግዱ ወደ ግለሰብ ተጠቃሚዎች በተናጠል እንዲሸጋገር በማድረግ በከፍተኛ ሁኔታ ተጽኖ አድርጓል፡፡ በዚህ የዲጂታል የመገናኛ ዘዴዎች በተስፋፉበት ዘመን በቅርብ ጊዜ እንደትልቅ ተግዳሮት እናስበው እና የማይደረስበት ይመስለን የነበረው ሁሉ በጣም ቀልሎ የንግድ ሰዎች የትም ሳይሄዱ ቴክኖሎጂውን በመጠቀም በየትኛውም የዓለም ክፍል በግዢ እና በአገልግሎት ዋጋ ላይ ውይይት አድርገው የሚወሰኑበት ደረጃ ላይ ተደርሷል፡፡

ስለዚህ አሁን በዓለማችን ውስጥ ካለው የለውጥ ማዕበል ጋር አብሮ በሚገባ ለመንሳፈፍ ድርጅቶች ትክክለኛ ስትራቴጂያዊ ዕቅድ ነድፈው ተግባራዊ ማድረግ አለባቸው፡፡ ይህ ካልሆነ ግን ድርጅቱ የሚመራበት ዋናው መሥመር ግራ የተጋባ እና ግምታዊ ጉዞ ስለሚሆን ያለስትራቴጂያዊ አስተሳሰብ መጓዝ ጉዳቱ ከፍተኛ ይሆናል፡፡

ይሁን እንጂ በስትራቴጂ ዝግጅት ሒደት ለሚያጋጥሙ ግራ መጋባቶች ብሎም ግድፈቶች ከሚጠቀሱ ዋነኛ ምክንያት ከድርጅቱ ስለ ስትራቴጂ

of an organization. Strategic plan development, which is the result of a structured strategic thinking process, helps to chart out the future course of action while at the same time providing the details of how to achieve them.

In this regard, the manner in which the process of strategic plan development is carried out is exceptionally important. This is because strategies have little contribution to organizational development and growth without a clear head and thinking process, which determines the quality of the plan. Strategic thinking requires a logical, systematic, and objective approach to find out what has changed, what is changing, and what will be changing in light of the aspiration of an organization. In the era of unparalleled change and least certainty, where nothing is going to settle down in the future, creating strategic knowledge and options is vital for gaining competitive advantage.

Especially, the mounting wave of changes and transformations taking place in the technological arena are not only transforming the human lives on earth but also they are highly influencing the way conventional business is done through transferring power from businesses to individual consumers. Today, because of the digital era, consumers are gaining strong ground to negotiate for the best price and service all over the world, which used to be a major obstacle in our recent memory. In order to successfully cruise through the current tide, organizations are thus required to develop and successfully implement strategic plans that withstand the test of the day.

Nevertheless, a major thread leading to the confusions and the loop holes in the strategy making process is much related to the organizational assumptions underlying strategic plan development. In some organizations, it has become commonplace to oversimplify strategic plan development and consider it as a one stop process to lasting organizational solutions. The development of effective strategic plan that works well in today's turbulent environment won't happen overnight. Strategic plan development is not a matter of hastily moving from mission development to strategic plan development to address or meet real organizational problems or needs.

Given the onset forces of change and the business dynamics, the challenges to developing effective strategic plans that visibly differentiate an organization from the standing crowd is increasingly compounding from time to time. Neither strategic plans are a simple box of gimmicks nor a bundle of

ዝግጅት ሂደት የሚሰጥ ግምታዊ አካሔድ አያልፍም፡፡ በአንዳንድ ተቋማት ሳይቀር የስትራቴጂ ዕቅድ ዝግጅትን አቃሎ ወይንም ሥራው በአንድ ጊዜ የሚያልቅ አድርጎ ማየት የተለመደ እና ለሁሉም ድርጅታዊ ጉዳዮች እንደብቸኛ ወሳኝ ነገር አድርጎ መውሰድ የተለመደ ነው፡፡ ይልቁንም ለዛሬው ፈታኝ ሥነ ምህዳር የሚያገለግል ውጤታማ የሆነ የስትራቴጂ ዕቅድ ዝግጅት በአንድ ሌሊት አይከሰትም፡፡ የስትራቴጂ ዕቅድ ዝግጅት ሲባልም ተቋማዊ ችግሮችን ለመቅረፍና ፍላጎቶችን ለማዳረስ እንዲሁ በችኮላ ከተልዕኮ አዘገጃጀት በመነሳት ወደ ስትራቴጂ ዕቅድ ዝግጅት የሚንደረደር ተግባር እንዳልሆነ መረዳት ያስፈልጋል፡፡

የቢዝነስን ተለዋዋጭነትና የለውጥ ኃይሎችን ያገናዘበ የተዋጣለት የስትራቴጂ ዕቅድ አዘገጃጀት የድርጅቶች ልዩነት ማሳያ ቢሆንም አዘገጃጀቱ ከነተግዳሮቶቹ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያየለ መጥቷል፡፡ የስትራቴጂ ዕቅዶች የሰዎችን ትኩረት መሳቢያ አልያም የመፍትሔ ስልቶች የተጠራቀሙበት ተቋማዊ ችግር መወጫ ብሎም ፍላጎት ማሟያ ማህደሮች አይደሉም፡፡ በመሰረቱ ውጤታማ የስትራቴጂ ዕቅድ ዝግጅት ጊዜና ጉልበት የሚፈልግ በእጅጉ የሚፈትንና አስጨናቂ መሆኑን ማጤን አስፈላጊ ነው፡፡ ውጤታማ የስትራቴጂ ዕቅድ ዝግጅት ብሎም አተገባበር በአንድ ድርጅት ውስጥ የዕቅድ አዘገጃጀት ሒደት ላይ  የሚተንራስ ሲሆን ስኬቱ ደግሞ በሥራ አመራሩ ቁርጠኝነትና ጉልህ ድጋፍ ላይ የሚመሰረት ነው፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ  አንዳንድ ድርጅቶች የስትራቴጂ ዕቅድ ዝግጅትን የተወሳሰበ አካሔድ እና አላስፈላጊ ጊዜና ገንዘብ የሚባክንበት እንደሆነ አድርገው ያዩታል፡፡ በዚህ ረገድ ስትራቴጂዎች የከፍተኛ የሥራ አመራር አካላትን ውሳኔና በርከት ያለ ተቋማዊ ሐብት የሚፈልጉ እምቅ ተግባራት መሆናቸውን አስፈላጊ ግንዛቤ እንደተነፈጋቸው ይስተዋላል። ስለዚህ በስትራቴጂ ዝግጅት ላይ የዋለ ጊዜና ሃብት ኢንቨስትመንት ላይ እንደዋለ መዋዕለ ንዋይ ተደርጎ ሊወሰድ ይገባል፡፡ በዚህ ተግባር መሰረታዊው ተግዳሮት የሚሆነው ተቋማት ያለምንም የሚባክን ወጪ ብሎም የተዘጋጀው የስትራቴጂ ሰነድ በመደርደሪያ ላይ አዋራና የሸረሪት ድር እንዳይወርሰው የዕቅዱ ዝግጅትን በቁርጠኝነት እና በስልት ማስኬድ አስፈላጊ ነው፡፡

ይህ ተግዳሮት በዋነኝነት የሚከሰተው ወሳኝ ባለድርሻ አካላት የስትራቴጂ ዕቅድ ዝግጅቱን እንዳላስፈላጊና በዕቅዱ ላይ የተቀመጡትን አዳዲስ ጅማሮዎቸ ለመቀበል ፍቃደኛ ሳይሆኑ ሲቀሩ ሲሆን በአንዳንድ ተቋማት ደግሞ የወቅቱ የስተራቴጂ ዕቅድ ዝግጅት ስትራቴጂአዊ ጉዳዮች ላይ ፈጠራ

**“በህይወት ጉዞ ውስጥ ማድረግ የምትችለው ሁለት ነገር ብቻ ነው፣ አንዱ ህይወት እንደመራህ መኖር ሲሆን ሁለተኛው ህይወትን ምቹ ወደ መሆን ቀይረህ በውስጡ መደሰት ነው።”**

ኸርማን ጄ ስታይንኸር

**“There are two things that you can do with life, you can either live it the way it is or you can make it comfortable and be glad in it.”**

Hermann J Steinherr

techniques that can be put together and readily be applicable to organizational needs or problems. It is important to understand that effective strategic plan development is profoundly challenging and painstaking, and at times emotionally and physically taxing. Thus, an effective strategic plan development and its implementation rides on how the strategy making process is managed within an organization, the success of which is largely credited to the unflagging commitment and support of the top management.

Yet other organizations see strategic plan development as a complicated process and even an expensive journey in terms of time and money. There appears to be lack of sufficient understanding that strategies are potential actions that require top management decisions and large amounts of organizational resources. So, time spent on strategic plan development must be considered as an investment in the future. The real challenge is, therefore, to perform strategic plan development seriously and systematically in the absence of which organizations have to always pay a high premium as the plan document is finally relegated to a shelf to gather dust.

This is especially the case when key stakeholders tend to resent or dismiss strategic plan development as irrelevant and are not willing to act on the initiatives of the plan. In some organizations, current views on strategic plan development seem to be inadequate to deal with the fast paced strategic issues in a more creative way. Thinking through strategic issues from a variety of angles of course needs sustained effort to understand and appreciate the underpinnings of strategy making process. This is imperative in order to lay the foundations that drive common understanding and commitment from key stakeholders.

Otherwise, organizations are most vulnerable in as much as they fail to involve key stakeholders at all phases of the strategy making process. Organizations thus better build and achieve common consensus around the need for strategic plan development in the hopes of improving their competitive position and ultimately their performance. Hence, soliciting an overall commitment of stakeholders must be the first step and the most important part of the strategy making process, whose absence may lead to different perception of a situation, fear of the unknown, conflicting opinions and motives, objectives and priorities, and so forth.

On the other hand, the strategic capability to turn information about the past into present knowledge

በታከለበት መንገድ በፍጥነት ለመተግበር በቂ እንዳልሆነ ስለሚታሰብ ነው፡፡ በእርግጥ በስትራቴጂአዊ ጉዳዮች ላይ ማሰብ የስትራቴጂ ዕቅድ አዘገጃጀት ሒደትን ቀጣይነት ባለው መልኩ መረዳትና ማበረታታትን ይጠይቃል፡፡ የዚህም ጠቀሜታ የሁሉም የባለድርሻ አካላትን የጋራ ግንዛቤ እና ጥረት ለማምጣት እንደ አንድ መሰረት ያገለግላል፡፡

ይህ ሆኖ ሳይገኝ ሲቀር ግን ድርጅቶች ወሳኝ ባለድርሻ አካላትን ማሳተፍ ባልቻሉበት መጠን በስትራቴጂ ዝግጅት ሒደት ውስጥ ለችግር የተጋለጡ ይሆናሉ፡፡ ስለዚህ ድርጅቶች የተወዳዳሪነት ብቃታቸውን ለማሻሻል በስትራቴጂ ዕቅድ አስፈላጊነት ዙሪያ የጋራ መግባባትን ማጎልበት ያንንም መፈፀም መቻል ይኖርባቸዋል፡፡ እንግዲህ በስትራቴጂ ዕቅድ አዘገጃጀት ሒደት ውስጥ የባለድርሻ አካላትን ቁርጠኝነት መጠየቅ ቀዳሚና በጣም አስፈላጊ ሲሆን ያለነሱ ተሳትፎ በማናቸውም ሁኔታዎች ላይ የተለያየ ግንዛቤን ሊያመጣ ስለሚችል ፤ ስለማያውቁት ጉዳይ ስጋት ውስጥ በመግባት የሀሳብ መነሾ ፣ በአላማ ፣ ቀዳሚ ትኩረት በሚሹ ጉዳዮች እና በመሳሰሉት ላይ ልዩነት ሊፈጠር ይችላል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ስትራቴጂአዊ አቅም ላይ በተመሰረተ መልኩ ያለፈውን መረጃ ዛሬ ላይ ወደ እውቀት ለመቀየር ለወደፊቱ ለሚኖሩ ፍላጎቶችና ተግባራት መሰረት ስለሚሆኑ ለስትራቴጂ ዝግጅት ሂደት እንደ ዋነኛ አዋጭ አካሔድ ይቆጠራል፡፡ በእርግጥም የተቋማት ዋነኛ ጥንካሬ እዚህ ላይ ነው፡፡ ተቋማት በአስቸጋሪ ወቅቶች የስትራቴጂ ውሳኔዎችን ለመወሰን

**"ውድቀትን የማያጣጥሙ ሰዎች ምንም ነገር የማይሞክሩ ናቸው፡፡"**
ኢልካ ቼዝ

**"The only people who never fail are those who never try."**
Ilka Chase

በሚያስችላቸው ግንዛቤዎችንና እውቀቶችን በመፍጠር ዙሪያ አቅማቸውን ቢያሳድጉ ይመረጣል፡፡ በተለያዩ የስትራቴጂ ዕቅድ ዝግጅቶችና ትግበራ ሒደቶች ውስጥ የሚያልፉ ድርጅቶች ብቁ ባለሙያዎችን ከማፍራት ባለፈ በስትራቴጂ አዘገጃጀት ሒደት እጅግ ተፈላጊ የሆነውን የፈጠራና አርቆ አላሚነትን ማዳበር ያስችላሉ፡፡ ለውጤታማ የስትራቴጂ ዕቅድ ዝግጅት ተግዳሮቶችን ለሚቀበሉ ድርጅቶች ሁልጊዜም ጠቀሜታው የጎላ ነው፡፡

ስለዚህ የአመራር ንቃተ ህሊናንና የስትራቴጂ ዝግጅት ሒደትን ማስተሳሰር ወሳኝ ነው፡፡ ብዙ ጊዜ በከፍተኛ የሥራ አመራር ቦታ ላይ ያሉ የሥራ ኃላፊዎች በአብዛኞቹ ድርጅቶች ማለት ይቻላል በተደጋጋሚ እንደሚሉት የነሱ ዋነኛ ሐላፊነት በስትራቴጂአዊ መንገድ ስለ ድርጅቱ የወደፊት እጣ ፈንታ ማሰብ ነው፡፡ ነገር ግን ይህ አባባል ውሃ የሚያነሳው ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎቹ በሙሉ ተግባር ፣ በከፍተኛ ተነሳሽነት ፣ አቅም እና ቁርጠኝነት ዕቅዱ ላይ ትኩረት ያደረጉበት ከሆነ ብቻ ነው፡፡ ሆኖም በፍጥነት እየተለወጠ ባለው ዓለም ውስጥ ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች ስትራቴጂአዊ አስተሳሰብን በድርጅቶቻቸው ውስጥ ምን ያህል ያንሸራሽራሉ የሚለው ጉዳይ እያደገ ያለ መሰረታዊ ክፍተት የሚታይበት የትኩረት አቅጣጫ ሆኗል፡፡

on which the foundation of future intentions and actions can profitably be based is central to the strategy making process. Indeed, one of the profound strengths of organizations lies here. Organizations better exert the maximum effort possible in creating the understanding and the knowledge base that is necessary to make strategic decisions at difficult times. Organizations going through rounds of strategic plan development and implementation don't only accumulate the in-house expertise but also develop the creativity and imagination that is much desired by the strategy making process. There are always benefits for organizations willing to accept the challenges of effective strategic plan development.

To this end, entwining the leadership mind with the strategic making process is crucial. It has been overheard while members of the top management, in most organizations, frequently conveying that their most important responsibility is to think strategically about the future direction of their organizations. This only holds water when the top management is fully and practically into it with great passion, energy, and commitment. There is a growing concern that a significant void still exists regarding how members of the top management are actually steering strategic thinking in their organizations in a world of such dramatic changes.

There are glaring and growing evidences that indicate that the seeds of effective strategy making process must be planted by embedding an adaptive culture that fosters creativity and strategic innovations. An adaptive culture is a major force that can drive an organization's ability to plan for the long term. An increasing number of organizations are gaining competitive advantage that positively impacts their strategic innovations owing to their ability to capture intelligence, transform it into usable information, and circulate it rapidly throughout their organization.

Generally speaking, there is a big push for being agile in order to take advantage of tremendous growth opportunities by way of great strides, strategic insight and flexibility, which is becoming one of the critical success factors in strategic plan development and implementation. To be strategically flexible on a continuing basis and to gain the competitive benefits of such flexibility, an organization has to develop the capacity to learn. So, the commitment and the role of top management in cultivating and nurturing the strategy making and implementation caliber can immensely help organizations to realize their vision and mission. There is no doubt that the creative

ውጤታማ የስትራቴጂ ዕቅድ አዘገጃጀት ሒደት ወደ ድርጅቱ በማዋሃድ ስትራቴጂአዊ ፈጠራ በታከለበት መልኩ እንደሚዘራ ቡቃያ እያደገ የሚታይ ማሳያ መሆን አለበት፡፡ ውህደት የመፍጠር ልምድ አንድን ድርጅት ለረዥም ጊዜ ማቀድ የሚያስችለው ዋነኛ ኃይል ነው፡፡ ስትራቴጂአዊ ፈጠራዎችን በመተርጎም ልቀት ያላቸው ክህሎቶች ተግባር ላይ ሊውል ወደሚችል መረጃ በመቀየር ሒደት እንዲሁም በፍጥነት እንዲሰራጭ በማድረግ በርከት ያሉ ድርጅቶች አንጻራዊ ጥቅም በማስገኘት በአዎንታዊ መንገድ ተፅኖ ማምጣት ችሏል፡፡

በአጠቃላይ ድርጅቶች ፣ እጅግ የላቀ እድገት እንዲያስመዘግቡና ቀልጣፋ አገልገሎት እንዲሰጡ ከፍተኛ ግፊት ያለ ሲሆን ለዚህም ፤ የስትራቴጂ ዕቅድ አዘገጃጀት እና አተገባበር ሒደት ዋነኛ የስኬት ምንጭ ተደርጎ መወሰድ አለበት፡፡ ቀጣይነትና ተከታታይነት ባለው አካሔድ በስትራቴጂአዊ አስተሳሰብ የሚገኝ አንጻራዊ ጥቅም ለማስጠበቅ አንድ ድርጅት ለመማር ዝግጁ መሆን መቻል አለበት፡፡ ስለዚህ የከፍተኛ ሥራ አመራር አካላት ቁርጠኛ ሚና የድርጅቱን ራዕይና ተልዕኮ በጉልህ ሊያሳካ የሚችለው የስትራቴጂ ዝግጅት እና ትግበራ ጥረት ማበረታታትና ማሳደግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

ይህን ሚና ተግባራዊ ለማድረግ በሚደረግ ጥረት የገብኮን ከፍተኛ የሥራ አመራር የቢዝነስ ስትራቴጂውን ከሀገሪቱ ሁለተኛ የአምስት አመት የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ጋር ለማስተሳሰር በማሰብ የአምስት አመት ስትራቴጂ ዕቅድ (እ.አ.አ 2016-2020) ነድፏል፡፡ እስካሁንም ኩባንያው ሊጠናቀቅ ጥቂት ወራት የቀሩት (እ.አ.አ 2012-2016) የራሱን የአምስት አመት ስትራቴጂአዊ መመሪያ ዕቅድ አውጥቶ ተግባራዊ ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ በመጠናቀቅ ላይ ባለው በዚህ የኩባንያው ዕቅድ ላይ የሰፈሩትን ግቦችና አላማዎች ስኬት ለመገምገም የአዲሱ ስትራቴጂ ዕቅድ መነደፍ ጠቃሚ ሆኖ ተገኝቷል ይህም ከኩባንያው መሰረታዊ ስትራቴጂ ዋልታዎች ጋር በማስተሳሰር በመጪዎቹ አመታት የኩባንያውን የላቀ ተወዳዳሪነት ለማስቀጠል ብሎም ለማሻሻል እንደሚረዳ ጥልቅ ግንዛቤ ተወስዷል፡፡

redefinition of markets and opportunities rests on the ability to develop effective strategic plans, which keeps an organization moving along with the changing world.

In an effort to fulfill this role, the top management of GEBECON PLC has developed a five year strategic plan (2016-2020) in order to realign its business strategy with the second GTP (five years strategic plan) of the country. So far, the company has been implementing its five years strategic plan (2012-2016) which is left with some months to complete. Preparation of the new strategic plan is found necessary to help the company to examine the goals and objectives achieved in the current strategic plan in order to redefine the company's strategic pillars that are necessary for maintaining and improving its competitive advantage in the years to come.

*References*


1. *David, F.F. (2011), Strategic Management: Concepts and Cases, Thirteen Edition, Pearson Education, Inc, USA*

2. *Wootten, S. and Horne, T. (2010), Strategic Thinking: A Nine Step Approach to Strategy and Leadership for Managers and Marketers, Third Edition, Kogan Page Limited, USA.*

3. *Glassman, M. A. et al. (2005), Thinking Strategically in Turbulent Times, M.E. Sharpe, Inc., USA.*

4. *Hitt, A. M. et al (2011), Concepts of Strategic Management: Competitiveness and Globalization, Ninth Edition, South-Western Cengage Learning, USA.*


**“ቀደም ሲል ሠርተህ ስላለፍከው ስራ በማውራት ጊዜህን አታባክን! ከዚያ ይልቅ አንድ ነገር በመሥራት ወይም በማቀድ ጊዜህን ተጠቀምበት።”**

ዩጂን ግሬስ

**“Don’t waste time talking about what you have already done. Use the time executing or planning something new.”**

Eugene Grace

# 12 ከሐረር ተለዋጭ አስፋልት መንገድ ፕሮጀክት የተወሰዱ ተሞክሮዎች
# Lessons From Harar-By-Pass Asphalt Road Project



**ሄኖክ መብራቴ**
ሐረር ባይ ፓስ መንገድ ሥራ ፕሮጀክት ሥራ አስኪያጅ
**Henock Mebrate**
Manager, Harar-By-Pass Asphalt Road Project

## 1. መግቢያ

የሐረር ተለዋጭ መንገድ ሥራ ፕሮጀክት በድርጅታችን ገምሹ በየነ ኃላ.የተ/የግል ኩባንያ እና በኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን መካከል በተደረገ የመንገድ ግንባታ ውል መሰረት እ.ኢ.አ. መስከረም 18/2006 ዓ.ም ተጀምሮ ሐምሌ 15/2008 ዓ.ም የተጠናቀቀ ፕሮጀክት ነው፡፡ ይህ ፕሮጀክት በምስራቅ ሀረርጌ በሀረሪ ክልላዊ መንግስት ውስጥ የሚገኝና 20.175 ኪ. ሜትር ርዝመት ያለው ሲሆን በኢ.መ.ባ የመንገድ ደረጃ DS3 በሚባል ስያሜ የሚታወቅ 7 ሜትር ስፋት እና 5 ሳንቲ ሜትር ውፍረት ካለው የአስፋልት ኮንክሪት ንጣፍ የተሰራ መንገድ ነው፡፡

ይህ መንገድ በሀረር ከተማ ውስጥ ያለውን የተጨናነቀ የትራፊክ እንቅስቃሴ በመቀነስ ወደ ከተማዋ ሳይገቡ አቋርጠው ወደ ሱማሌ ክልል እና ሱማሊያ ሀገር የሚሄዱ ተሽከርካሪዎችን በተቀላጠፈ ሁኔታ ያስተናግዳል ተብሎ ይጠበቃል፡፡

የመንገዱ ርዝመት አነስተኛ ቢሆንም እንኳን በአብዛኛው ኮረብታማ በሆነ መልከዓ ምድር የሚያቋርጥ በመሆኑ ምክንያት በዋነኛነት መጠነ ሰፊ የሆነ (950,000 m3) የቆረጣ እና (485,000 m3) የአፈር ሙሌት ስራዎችን ያካተተ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ 3 ድልድዮች 30 የውኃ ማስወገጃ ቱቦዎች እንዲሁም ከ 80,000 m2 በላይ የድንጋይ ንጣፍ ያላቸው ዲቾች እና የመንገድ መሸርሸር መከላከያ ሥራዎች ተሰርተዋል፡፡ የዚህ መንገድ ባለቤት የሆነው የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን ለመንገዱ ግንባታ ብቻ ወደ 450 ሚሊየን የሚጠጋ ብር ወጪ አድርጎበታል፡፡ ይህንኑ ሥራ በተቀለጣፈ ሁኔታ ለማከናወን ድርጅቱ አንድ አዲስ ክሬሸር የአስፋልት ባቺንግ ፕላንት እና አዳዲስ ዋገን ድሪል ለፕሮጀክቱ ገዝቶ ሥራ ላይ አውሎአል ፡፡

## 1. Introduction

A contract agreement has been signed between our company, Gemshu Beyene Construction PLC, and the Ethiopian Roads Authority (ERA) on 27th February, 2013 for construction of Harar-By-Pass road Project and the project has been substantially completed on 22th July, 2016. This road project is located Harari National Regional State around Harar Town. The road consisted construction of 20.175km which is designed and built as per the ERA Road class of DS3 (ERA's Geometric Design Manual) with a 7m width and 5cm Asphalt Concrete thickness.

This road project is believed to resolve the road-traffic conjunction seen in the city of Harar by providing alternative route to Somali National Regional State and to the neighboring Somalia with no need to enter into the city of Harar.

Though the length of the road is short, most of the construction work has been carried out along mountainous terrain of landscapes. For this reason, the construction had massive excavation works of 950,000m3 and 485,000m3 fill works including construction of 3 bridges, 30 culverts and more than 80,000m2 paved ditches as well as road protection works. The employer, Ethiopian Roads Authority (ERA), has invested about ETB 450 million for project work. The contract has mobilized one new 150 ton crusher, one mobile asphalt batching plant and high capacity wagen drills for implementation of the work.

## 2. አጠቃላይ የፕሮጀክታችን የሥራ ክፍሎች አደረጃጀት

ድርጅታችን የዚህን መንገድ ግንባታ ውል ፈፅሞ ወደ ሥራ በገባበት ወቅት ከዚህ ቀደም ሠርቶ ባጠናቀቃቸው ትላልቅ ፕሮጀክቶች ላይ መሠረታዊ ልምድን ያዳበረበት እና ወጥ የሆነ ሥራ ማስኬጃ ሲስተም በሁሉም ፕሮጀክቶች ላይ እየተገበረ በነበረበት ወቅት በመሆኑ ይህንን ፕሮጀክት ለማከናወን በአደረጃጀት በኩል የገጠሙት ተግዳሮቶች አልነበሩም። ስለዚህም የፕሮጀክታችን ዋና ዋና የሥራ ክፍሎች በተገቢው ሁኔታ የተደራጁ እና የየራሳቸውን ሥራ በአግባቡ ሊወጡ በሚችሉበት ሁኔታ የተዋቀሩ ሲሆን በሰው ኃይል አደረጃጀታቸውም በኩል ከሰው ኃይል አስተዳደር እና ከመሳሪያዎች ጥገና ክፍሎች በስተቀር ሌሎች ክፍሎች በብቁ ሁኔታ የተደራጁበት ፕሮጀክት ነው ማለት ይቻላል፡፡

## 3. የፕሮጀክታችን የሥራ አፈፃፀም

ከላይ በተገለፀው መሰረት የተደራጀው ፕሮጀክታችን በሥራ አፈፃፀሙ በኩል ከነበሩበት የተለያዩ ጫናዎች እና የወሰን ማስከበር ችግር እንዲሁም የዲዛይን መለዋወጥ አኳያ የሥራ አፈፃፀሙ በጣም ጥሩ የሚባል ነው ፡፡

የፕሮጀክታችን የሥራ አፈፃፀም ውጤታማ እንዲሆን ካደረጉት ዋንኛ ምክያቶች ውስጥ ድርጅታችን እንደ መመሪያ አድርጎ የሚከተለው ሥራን በሁለት መንገድ በማቀድ ዋና (Master Schedule) ዕቅድ እና ውስጣዊ (Internal Schedule) እቅድ ሁለት በማለት ግቦችን አስቀምጦ በተለይም ውስጣዊ እቅዱን ተግባራዊ ለማድረግ ያላሰለሰ ክትትል በማድረግ፣ የሥራ ሂደቶችን በየወቅቱ በመገምገም እና አስፈላጊውን የእርምት እርምጃዎች በመውሰድ የሥራው ባለቤት በዋና ዕቅዱ መሰረት ሥራው ተጠናቆ ሊረከብ ከሚጠበቅበት ጊዜ ቀድሞ በማጠናቀቅ ሥራን የማስረከብ ስትራቴጂው ነው፡፡

የፕሮጀክታችን ሰራተኞች ባጠቃላይ እንዲሁም የአንበሳውን ድርሻ የሚይዙ የመሳሪያ ኦፐሬተሮች ባደረጉት ጥረት እና የዋናው መስሪያ ቤት የሥራ ኃላፊዎች ለፕሮጀክቱ ትኩረት ሰጥተው በዕቃ አቅርቦት እና በገንዘብ በኩል ከፍተኛ እገዛ በማድረጋቸው የፕሮጀክታችን ሥራ በጥሩ ሁኔታ የተካሄደ ሲሆን ፕሮጀክታችን በፈለግነው ሁኔታ ባይሆንም እንኳን ያጋጠመውን የሥራ መሰናክሎች ተቋቁሞ ከተሰጠው ተጨማሪ ጊዜ በፊት አጠናቋል፡፡ በዚህ ረገድ በፕሮጀክቱ ላይ ያጋጠሙ ያልተጠበቁ መሰናክሎችን መዳሰሱ ጠቃሚ ነዉ፡፡

## 4. በፕሮጀክቱ ሥራ ላይ ያጋጠሙ ተግዳሮቶች እና የተወሰዱ እርምጃዎች

በፕሮጀክታችን የሥራ ሂደት ላይ ከገጠሙን አስቸጋሪ ችግሮች መካከል በዋነኛነት የሚጠቀሱት የሚከተሉት ናቸው

፩ኛ. ፕሮጀክታችን በሚያልፍባቸው ወረዳዎች ውስጥ ከፍተኛ የሆነ የእርሻ መሬት እጥረት ያለ ሲሆን ነዋሪ አርሶ አደሮች ከካሳ ክፍያ እና ሌሎች የመንገዱ ዲዛይን ከፈጠራቸው ችግሮች በመነሳት ቅሬታቸውን ለመግለፅ ሥራን በኃይል የማስቆም ልምድን እንደ መፍትሄ ማግኛ መንገድ በመውሰዳቸው በየዕለቱ /በየጊዜው/ ሥራ የሚቋረጥባቸው አጋጣሚዎች የፕሮጀክቱን የሥራ ሂደት ካጓተቱት እና ፕሮጀክቱን ከተፈታተኑት ችግሮች ውስጥ የአንበሳውን ድርሻ ይወስዳሉ፡፡

## 2. Organization of Project Work

Our company has signed the project contract and started the work at the right time following completion of two major projects. It was at that time that the company has been establishing constant administration system in all projects which helped to resolve any challenges toward the organization of the project. Therefore, major units of the projects were properly organized except human resource management and equipment maintenance departments, which needed close follow up from project and head office.

## 3. Performance of the Project

As described here above, under critical right of way problem and design shortfall of the project, the project is completed with satisfactory performance. One of the major reasons that made the project successful in this sense is due to the planning principle followed by the company. Apart from the Master Project Schedule as provided in the contract agreement, the company develops its own Internal Project Schedule with a much shorter duration against which project progresses are evaluated and every necessary measures are taken in order to deliver the project work to the employer prior to the contact time.

In an effort made by workers of our project in general and the machine operators who take the lion's share; as well as the full attention paid to the project by top management at the head office in material supply and provision of finance, the project has been successfully completed.

## 4. Challenges of the Project and Measures Taken

Some of the major challenges and impediments to complete the project within the specified contract period include:

1. Due to economical land-use character and scarcity of farm land in the Woredas where the project road traverses, possession of land required for the work has instigated lots of dreadful scenarios. Owing to demands often raised by the local people, there was a frequent interruption of the project activities at different times which has the lion's share putting the project in a serious challenge and affecting progress of the work

2ኛ. መጠኑ አነስተኛ ነው ተብሎ የታሰበ ነገር ግን ከታሰበው ውጪ የሆነ እና አቅምን ገድቦ መስራት በሚያስገድድ ቦታ ላይ ያጋጠመን በተፈጥሮው ጠንካራ እና አቀማመጡ ድርብርብ ንጣፍ የሆነ የድንጋይ ቁፋሮ ስራ የፕሮጀክታችንን የሥራ አፈፃፀም በከባድ ሁኔታ ተፈታትኖታል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ለእንዲህ አይነቱ አስቸጋሪ ሥራ ተመጣጣኝ ቴክኒካል እውቀት ያለው የፈንጂ ኤክስፐርት የሚፈልግ ሆኖ ሳለ ሥራውን በፕሮጀክቱ ላይ በተለያዩ ጊዜያት ለመስራት ተመድበው የነበሩ የፈንጂ ባለሞያዎች ካላቸው ዕውቀት እና ልምድ በላይ ዕውቀትን በመጠየቁ  የስራ ሂደቱ እንዲጓተት እና አድካሚ እንዲሆን አድርጎታል፡፡

3ኛ. ለኮንትራክተሩ የተሰጡት የሥራ መመሪያዎችና ዲዛይን የተሟሉ እና ጊዜን የጠበቁ ባለመሆናቸው የሥራ ግብአቶችን እና የሰው ኃይል ጭማሪን የሚጠይቁ ወይንም የሥራ ጊዜን የሚያራዝሙ፣ ተጨማሪ የስራ ትዕዛዞች የሚሰጡ በመሆናቸው የሥራውን እንቅስቃሴ ለመቆጣጠር እና አቅጣጫ ለማስያዝ አስቸጋሪ ሁኔታን ከመፍጠሩም በላይ ፕሮጀክቱ እንዲጓተት የበኩሉን ድርሻ አበርክቷል፡፡

እነዚህን ችግሮች ለመፍታት የፕሮጀክቱ ሠራተኞች በሙሉ ያላሰለሰ ጥረት አድርገዋል፡፡ በተለይም ከአማካሪ መሀንዲሱ ጋር በመወያየት አብዛኛዎቹ የሥራ መመሪያዎች እንዲሟሉ ለማድረግ ተችሏል፡፡ በዋናው መስሪያ ቤት በኩልም በተለይም የድንጋይ ቁፋሮ ሥራ ከታሰበው ውጪ መሆኑን እና የድንጋዩ ባህሪይ የተለየ መሆኑን እንዲሁም ሥራው የሚሰራባቸው ቦታዎች ጥንቃቄ ሊደረግባቸው የሚገባ መሆኑን በመገንዘብ ሥራው በተቀላጠፈ ሁኔታ እንዲሰራ ለማድረግ በየወቅቱ የፕሮጀክቱን አካሄድ በመከታተል አስፈላጊ የሆኑትን መሳሪያዎች በመመደብ እና አዲስ ዘመናዊ የድንጋይ መሰርሰሪያ ገዝቶ በማቅረብ የፕሮጀክቱን አፈፃፀም ለማቀላጠፍ ተገቢውን እገዛ አድርጓል፡፡

በተጨማሪም ከአካባቢው የመንግስት ሥራ አስፈፃሚ አካላት ጋር በፕሮጀክት ደረጃም ሆነ በዋናው መ/ቤት በኩል ቅርርብ በመፍጠር ህብረተሰቡ በፕሮጀክቱ ላይ የሚፈፅመውን የሥራ ማስቆም ተግባር እንዲተው ለማድረግ ጥረት ተደርጓል፡፡ ይህም ችግር በተወሰነ መልኩ ሊቃለል ቢቻልም ፕሮጀክቱ እስከተጠናቀቀበት ዕለት ድረስ ሥራ የማስቆም ተግባሮችን ሙሉ በሙሉ ለማስቀረት አልተቻለም፡፡

## 5. ከፕሮጀክቱ የተገኙ ተመክሮዎች

ፕሮጀክታችን በመጠን አነስተኛ የሆነ ቢመስልም እንኳን ወደር የለሽ አስተምህሮዎችን ለድርጅታችን ያበረከተ መሆኑ አሌ የሚባል አይደለም በተለይም፡-

1ኛ. ድርጅታችን ማንኛውንም ፕሮጀክት በሚጫረትበት ወቅት ስለ ሥራው ብቻ ሳይሆን ሥራው በሚገኝበት አካባቢ ያለው ህብረተሰብ አመለካከትና የሥራ ባህል በማጥናት ወደ ስራ በሚገባበት ወቅት ከህብረተሰብ የሚነሱ ተግዳሮችን ሊያስወግድ በሚችልበት መልኩ ፕሮጀክቶችን ማደራጀት እንዳለበት፡፡ እንዲሁም

2ኛ. ድርጅታችን በየትኛውም ሁኔታ ድርጅቱን በሚጠቅም መልኩ ሥራን የሚያስፈፅሙ ባለሞያዎች በመያዝ በተለይም ከአማካሪ መሀንዲስ የሚሰጡ ዲዛይኖችን፣ የሥራ ትዕዛዛትን ጠንቅቆ በመመርመር ወደ ተፈፃሚነት ከማምራት በፊት መስተካከል ያለባቸውን እንዲስተካከሉ በማድረግ ድርጅታዊ ጥቅምን የሚያስከብር አቋም መገንባት እንዳለበት። እንዲሁም

2. Nature of rock, formation of layer in rocks and type of rock excavation (Controlled blasting) were the major challenges affecting progress of the work. In addition to that, rock excavation with controlled blasting requires precision in using the amount of explosives; it needed an explosive expertise with an extra ordinary experiences and deductions.

3. Design provision and work instructions provided to the contractor were incomplete and late and as a result  planning of the works with the required resources were so difficult and affected progress of the work and need extra efforts of the contractor.

In order to overcome these problems, staff members of the project had their unreserved effort especially in consultation with the Consultant, design and incomplete instructions were resolved with time. The head office has paid immense follow-up to the project completion; especially with regard to the rock excavation which was beyond the expectation and understanding character of the rock along care that should be taken at the project site with assignment of necessary equipment that include high capacity wagen drill machine. In connection, the Company has made all possible efforts to liaison with local administrative officials and nearby farmers to overcome the right of way and disruption problem of the project.

## 5. Lessons Learned

Even though the project seems to be small in size, it is undeniable fact that there are remarkable lessons that can be learned from the project undertakings, especially;

1. GEBECON Plc while bidding for any project has to investigate not only about the work but also about the perception, work culture and livelihood in that specific community in order to organize the project in such a way to handle preventable challenges during project work.

2. Furthermore, the Company has learned that it has to engage experts who can analytically investigate designs and instructions coming from the Consultant for possible correction before their implementation.

3. The Company has to work with local administration and local people in harmonious manner to support the project

3ኛ. ከአካባቢው ማህበረሰብና መስተደዳር ጋር ቅርበት በመፍጠር ሥራውን እንዲያግዙ ማድረግ፡፡ እንዲሁም

4ኛ. በመሣሪያዎች ደህንነት ጥገና እና አቋም ማስተካከል ሥራዎች ላይ የሚታየውን ከፍተኛ ክፍተት ድርጅታችን የተደራጀ ክፍል በማቋቋም ከፍተኛ ወጪ ወጥቶባቸው የተገዙ መሣሪያዎቻችንን ወደ ተሻለ አቋም በማምጣት በተመሣሣይ እና ተደጋጋሚ ጥገናዎች ምክንያት የሚባክኑ ወርቃማ የሥራ ጊዜያትን በማስቀረት የፕሮጀክቶችን የሥራ አፈፃፀም ማጎልበት እንዳለበት ከምን ጊዜውም በላይ በሀረር ተለዋጭ መንገድ ሥራ ፕሮጀክት ላይ የተማረባቸው ዋና ተስተምህሮቶች ናቸው ብለን እናምናለን፡፡

## 6. ምስጋና

በፕሮጀክታችን ስራ ላይ ተመድበው ሲሰሩ የነበሩ ሰራተኞች እና ከፕሮጀክቱ ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ግንኙነት ያላቸው የዋናው መ/ቤት ኃላፊዎችና ሰራተኞች ባደረጉት ጥረት ፕሮጀክቱ ከፍጻሜ የደረሰ ሲሆን ለፕሮጀክቱ ውጤታማነት ላበረከቱት አስተዋፅኦ ከፍተኛ ምስጋና በመላው የፕሮጀክቱ ሠራተኞች ስም አቀርባለሁ፡፡ እንዲሁም የአማካሪው ድርጅት እና የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን ላደረጉልን ድጋፍ ሁሉ ምስጋናችንን እናቀርባለን፡፡

4. Additionally, Harar-By-Pass asphalt road project has also thought us the need for modern equipment and machinery renovation workshop to improve compatibility of the existing equipment acquired with huge capital outlay and to avoid repetitive breakdowns and maintenance, which entails additional cost of time and working outside schedule.

## 6. Acknowledgment

We thank sincerely those staff members who have been working with our project and staff members from the head office who are connected to the project for the commitment they have displayed toward the successful completion of the project. We would also like to thank the Consultant Company and the Ethiopian Roads Authority (ERA) for their support on the project.



*Harar-By-Pass Road Project Team*

# 13 ኢሊሊ ኢንተርናሽናል ሆቴል : በላቀ አፍሪካዊ መስተንግዶ
# Elilly International Hotel: Redefining African Hospitality

## 13.1 ቃል የምንገባው ...

ፈጠራን ማበልፀግ ፣ ጥልቅ አስተሳሰብን እና ዓለም አቀፋዊ አንድነትን ዕውን ማድረግ የወቅቱ የዓለማችን የትኩረት አቅጣጫ ሆኗል፡፡ ኢሊሊ ኢንተርናሽናል ሆቴል እንደ አንድ የአገልግሎት አቅራቢ የተቋማትን ቅርፅና ይዞታ እየለወጠ ባለው የማያቋርጥ የዓለም የውድድር ዑደት ውስጥ ተነጥላ የማይትታይ ናት፡፡ በኢሊሊ እንደ አንድ ዓለም አቀፍ ተቋም ሊኖረን በሚገባው ሚና የሁሉም ባለድርሻ አካላት ተቋማዊ ቁርጠኝነት ፣ ተነሳሽነትና የላቀ ፍላጎት እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡

ዛሬ የአዲስ አበባን ሆቴሎች በመምራት ላይ ያሉ በዘርፉ የላቁና የበቁ ባለሙያዎችን በመፍጠሯ ኢሊሊ ትልቅ ኩራት ይሰማታል ። በኢንደስትሪው እያደገ በመጣው የመስተንግዶ እና ማህበራዊ ሥነ-ምህዳር ሁሉን አቀፍ የመስተንግዶ ውድድር ውስጥ በእውኑ ኢሊሊ የላቀ የመስተንግዶ መገኛ ማዕከል ናት፡፡

ይቺን ሀገር በቀል ነገር ግን ዓለም አቀፍ የሆቴል አርማ/ብራንድ ወደሚገባት የላቀ የመስተንግዶ ማማ ላይ ለማድረስ በምናካሒደው የኢሊሊ ፕሮጀክት ጥረት ሁሉም ባለድርሻ አካላት በተባበረ ክንድ እንዲሳተፉ እንጋብዛለን ። የመግባቢያ ቋንቋዎቻችንም “ሁለንተናዊ መስተንግዶ!” ፣ “የጋራ ምክክር!” እና “በጋራ እናስተጋባለን!” የሚሉ ናቸው፡፡

ግልጽ ፣ ተአማኒና ገንቢ በሆነ መልኩ በተከታታይ የምናካሒዳቸው ግንኙነቶች ለሰራተኞቻችን እና ለደንበኞቻችን ደህንነት መጠበቅ እንደ አንድ ዋነኛ ጉዳይ ጠንካራ መሰረት ሆነዋል፡፡

## 13.1 Our Promise...

Today's world focus is on cultivating innovation, critical thinking and the realization of global citizenship. Elilly Hotel, as one and a part of world's service rendering institutions, cannot be indifferent to the never-ending global competition that is shaping the fate of institutions. For the role that we must play as a global institution, the dedication, commitment and passion of every stakeholder is a. Sine qua non. Elilly has the honor of producing great and exceptional minds who have made their marks and who today occupy the commanding heights of Hotels in Addis Ababa. The growing Hospitality and social landscape within and outside award winners in the hospitality industry and captions of industry who constitute the alumni of this, our Institution, Elilly truly is a citadel of hospitality excellence. We, therefore, invite all stakeholders in the Elilly project to join hands with us in the task of putting this indigenously built International Brand Hotel on the front row of hospitality excellence where she belongs.

The language of our engagement is "inclusive HOSPITALITY," "Consultative approach," and "Wemantra". Our strongest promise is found within the foundations of our radically and consistent engagement in open; honest and constructive



*Elilly Intl. Hotel Management Comittee*

እነዚህ ለኢሊሊ አርማ ከፍታ የሚመጥኑ መሃላዎቻችን ናቸው ፤

- ለኢሊሊ ብራንድ በማህበራዊ መንገድ የሚተገበር እንዲሁም ዓለም አቀፋዊ ዕውቅና የተቸረው የላቀና ጥራቱን የጠበቀ ሥልጠና በመስጠት ብቁ የመስተንግዶ ሙያተኞችን ማፍራት ፤
- የአሰልጣኞቻችን መሰባጠር ፤
- ከወቅቱ የሀገር ውስጥ እና ዓለም አቀፍ ተጓዦች ፍላጎት ጋር የሚመጣጠን  የአገልጎሎት ደረጃ ማሻሻል ፤
- የዕድገት ፍላጎታችን እንዲሳካ የኢሊሊን ብራንድ በተገቢው መንገድ ማነፅና በተረጋጋ መልኩ ማስኬድ ፤
- ዓለም አቀፉን የመስተንግዶ ግንዛቤያችንን የበለጠ ለማስፋት ትብብር መፍጠር ፤
- እንደ አንድ ስትራቴጂ ቅድመ ሁኔታ ከሁሉም የመስተንግዶ መዳረሻዎች ጋር የኢንደስትሪ ትስስር መመስረት ፤
- የመስተንግዶ ጥበብ ፈጠራ ማዕከል መሆን ፤
- የሰው ኃይል ቡድናችንን የኩራት ምንጭ ማድረግ ፤
- የመስተንግዶን አቅም ግንባታ መሞከር እና ተቋማዊ ማድረግ ፤
- በኢሊሊ ብራንድ ልቆ መገኘት ፤
- መስተንግዶን የጋራ መግባቢያ ማድረግ፡፡

## 13.2 ኢሊሊ ኢንተርናሽናል 5 ኮኮብ ሆቴል

### በምን እንለያለን?

የመስተንግዶ ልኬት ወደሚፈካበት ኢሊሊ ኢንተርናሽናል ሆቴል እንኳን ደህና መጡ፡፡ ኢሊሊ ትክክለኛው የአገልግሎት ጥራት የተሟላበት መስተንግዶና ተመጣጣኝ ዋጋ ፈልገው የሚመጡ ደንበኞችን ለማገልገል ትተጋለች፡፡ የኢሊሊ ባለሚሎች በራስ መተማመንና ፍጹም ምቹ በሆነ ስሜት ውስጥ በመሆን 'እነሆ ስለ ሁሉም ብቁ ነን' ብለው እንዲናገሩ ለማስቻል የላቀ መስተንግዶ አቀራረብ መመሪያ ሆኖናል፡፡ ኢሊሊ ሁሉም አገልግሎት አሰጣጥ በአንድ ወጥ የአቀራረብ መንገድ አይተገበርም ብላ ታምናለች፡፡ ግባችን ደንበኞቻችን ከእኛ ጋር በሚያደርጉት እያንዳንዱ መስተጋብር ውስጥ አዎንታዊ የአገልግሎት ልዩነትን ማሳየት ነው፡፡ ወደ ዘርፉ በመጣንበት አጭር ጊዜ ውስጥ የደንበኞቻችንን ፍላጎት በላቀ መልኩ ማረጋገጥ እንደምንችል በማመን ለመስተንግዶ ተልዕኮአችን ፍልስፍና ተግባራዊ መሆን ተግተናል፡፡

ምንም እንኳን በተወሰነ መልኩ የመስተንግዶ ጥበብ በትምህርት ይገኛል ብለን ብናምንም ሁላችንም ግን ከሆነ ልዩ ብቃት ጋር አብረን እንደምንወለድ ሁሉ የመስተንግዶ ክህሎትም በውስጣችን አብሮን ተፈጥሯል፡፡ በዕዝነ ልቦናችን አልያም በውስጣችን እየተመራን በልምምድ ፣ በመመሰጥ ብሎም በጥረት እንደምናከናውነው ሁሉ መስተንግዶም የነዚህ አካሔድ አካል ነው፡፡ ልክ በኢሊሊ ለእንግዶቻችን ማቅረብ እንሚጠበቅብን መስተንግዶ አይነት ሁሉ ሳናውቀው በዕለት ተዕለት ህይወታችን ትህትናውን እንኖረዋለን፡፡ መስተንግዶ በቤት ውስጥ ጀምሮ

communication on critical issues bordering on welfare of staff and clients, the provision of top quality of training that will produce Hospitality graduates whose qualifications are socially applicable to Elilly Brand and internationally recognized brands; the diversity that should characterize our Trainers; how to enhance and improve on the relevance of our existing service standards in line with current national and International traveler needs; how to revamp and stabilize our Elilly Brand to meet our development needs; how to deepen our international hospitality understanding and collaboration; how to make industry partnerships with all hospitality places a strategic priority; how to become a hub for hospitality knowledge creation and innovation; how to turn our team of manpower to place of pride; how to check and institutionalize hospitality capacity building, excellence in Elilly Brand, search for hospitality citizenship overall, how to ensure that our dear brand worth its name. This is our promise to Elilly Brand.

## 13.2 Elilly International 5 Star Hotel

### Why we are Different?

Welcome to Elilly International Hotel where Luxury is in the making. Elilly is bound to redefine hospitality for customers who expect the right quality service at the right price. The notion of Luxury guided us to train Elilly associates to gain self-confidence and feel comfortable to say to our customers, we thought of everything. Elilly believes that one set-up of service does not fit all. Simply our goal is to make positive difference in our customers' life, in every contact they make with us. In our short existence, we endeavor this philosophy hoping that our hospitality mission will guarantee and exceed our customer expectations.

Although some time we believe Hospitality cannot be trained in anyone; we are all born with the skill of Hospitality, within us as we are born with certain talent. But as we all only use our common sense, and practice, meditation and efforts so is Hospitality. We perform Hospitality in our daily life without even realizing that it's the same hospitality we are expected to deliver to our guests at Elilly. Hospitality starts at Home, gets refined in one's Work Place and develops with one passing one's experience to Others. Here is what we know before we start as a career in this great Industry:

*The Respect shown to our elders,*
*Offering our seat to Elders in a bus or Train,*
*Helping a disabled Person to Cross the street,*
*Visiting a sick friend or relative, and many more ......*

በሥራ ቦታ እየጠራ በመሔድ ከአንዱ ወደ ሌላው በተሞክሮ እያደገ ይተላለፋል፡፡ በዚህ ግዙፍ ኢንደስትሪ ውስጥ ከመሳተፋችን በፊት ከምናውቃቸው የትህትና መገለጫዎቻችን ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ያህል ፤ ለታላላቆቻችን የምናሳየው አክብሮት ፣ ለታታላቆች እና ለአቅመ ደካሞች መቀመጫ መልቀቅ ፣ አካል ጉዳተኞችን መርዳት ፣ ወዳጅ ቤተ ዘመድ ጥየቃ እና ሌሎች ተጠቃሽ ናቸው፡፡

ይህንን ባህላዊ የሰው ልጆች መገለጫ ከዓለም አቀፍ ነባራዊ ሁኔታዎች ጋር በአንድ ላይ ስናስተሳስረው ዘመናዊ አገልግሎት ሊሆን መቻሉን እንረዳለን፡፡ ለዚህም ነው የኢሊሊ ራዕይ እውነተኛ መስተንግዶ በማቅረብ በላቀ የአገልግሎት ጥራት ደረጃ ልዩነት በመፍጠር ቀዳሚ ምርጫ የሚያደርጉን ደንበኞች ማፍራት የሆነው፡፡

እየፈኩ ያሉ ከዋክብቶቻችን የኢሊሊን አርማ ይዘው ይጓዛሉ

## 13.3 ማረፊያ ክፍሎች

እጅግ ዘመናዊ የሆኑት ሁሉም የኢሊሊ 155 የሆቴሉ ክፍሎች ምቹ በቁሳቁስ ተሸሞንሙነው ኃሴት ሲያላብሱ በመስታወት የተሰሩት መታጠቢያ ክፍሎች ደግሞ የህዋ ላይ ድባብ ይፈጥራል፡፡

## 13.4 ባርና ሬስቶራንት

### ኤስ ኤን ኤስ ዋና ቡፌ ሬስቶራንት

ቁርስ ፣ ምሳ ፣ እራት እና ቡፌ ተከሽኖ በሚቀርብበት በሆቴሉ ዋና ሬስቶራንት ሁሉም አንድ ልዩ ጣእም ያጣጥማል፡፡

### ኢሊሊ ልዩ (VIP) ሬስቶራንት

በሀገራዊ እና ዓለም አቀፋዊ የምግብ አዘገጃጀት ታጅቦ በጣልያን ጥዑመ ልኬት ይከሽናል፡፡

### ዘርፈ ብዙ የስፖርትና ፑል ባር

ቀዝቀዝ ባሉ መጠጦች ዘና ብለው ባሻዎት የመጠጥ ምርጫ ፍላጎትዎን ያረካሉ፡፡

በትላልቅ የቴሌቪዥን ስክሪኖች በዓለም ዙሪያ ያሉ ስፖርታዊ ውድድሮችን በስፖርት ባር እየተዝናኑ ይመለከታሉ፡፡

### ማርስ ክለብ

ከምሽት ሙዚቃ ዝግጅት ጋር አፐሪቲፍ እና ኮክቴል እየተጎነጩ በምርጥ የሙዚቃ ድባብ ዘና ይላሉ፡፡

### ኮዚ ባር

የተለያዩ ለስለስ ያሉ መጠጦችን እየተጎነጩ ዘና በሚያደርጉ ሙዚቃዎች መንፈስዎን ያድሳሉ፡፡

### ተጨማሪ አገልግሎቶች

- ዓለም አቀፍ ደረጃቸውን በጠበቁ የስብሰባ አዳራሾች የኮንፍረንስ አገልግሎት መስጠት

Therefore, when we squeezed this traditional mankind custom together and refined in global context then we get what we call modern service. That is why Elilly's vision is simple; to provide authentic hospitality by making a difference in the lives of the people we touch in order to be our Clients' first choice in hospitality!!



*Elilly Rising Stars Groomed to Uphold its Brand*

## 13.3 Accommodation

All 155 rooms are modern, furnishings and fabrics are in light earth tones that sooth the soul, while the glass enclosed bathrooms create atmosphere in the space.

## 13.4 Restaurant and Bar

### SNS Main Buffet Restaurant

Something for everyone tastes at the hotel main restaurant serving breakfast, lunch, dinner, and buffet service with action cooking.

### Elilly VIP Restaurant

Happenings and inspired by local and international cuisine. It is a getaway to the flavors and tastes of the Italian specialties.

Refresh yourself with a cool drink or please your appetite with something small by the pool. Watch different types of sport game in the world at unison sport bar with big screen TV.

### Unison Sport and Pool Bar

### Mars Club

With a Night Live Music, sip aperitifs and cocktails, and get relished with the views and hit it off at the area Mars club.

- ስፓ እና ሳውና
- የጂምናዚየም አገልግሎት
- ነፃ Wi-Fi
- ቢዝነስ ማዕከል
- የልብስ እጥበት አገልግሎት
- ምቹና ዘመናዊ መኪና ማቆሚያ
- የጉዞና የጉብኝት ወኪል
- የባንክ አገልግሎት
- የምንዛሬ ቢሮ
- መገበያያ ማዕከላት
- ጌጣ ጌጥ መሸጫ እና ሌሎችም

## Cozy Bar

Enjoy soft music and different types of cool drink.

## Services

- Conference service with fully furnished international standard hall
- Spa and sauna
- Gym
- Free Wi-Fi
- Business center
- Laundry services
- Modern valet car parking
- Travel and tour
- Bank and currency exchange services
- Shopping centers
- Souvenir shops, and so forth.











## 13.5 ለሆቴሉ የተሰጡ ሽልማቶች

በተባበሩት መንግሥታት የቱሪዝም ድርጅት የሆቴሎች ኮከብ ምዘና ውጤት መሠረት ኢሊሊ በኢትዮጵያ ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የ"5 ኮከብ" ደረጃ ዕውቅና ተሰጥቶታል፡፡ ይህ በሀገሪቱ ለሆቴሎች የተሰጠ ትልቁ የኮከቡ ደረጃ ክብር በላቀ አቅርቦት ፣ አገልግሎት ፣ የሰው ኃብት ብቃት እና ሁሉን አቀፍ የደንበኞች እርካታን መሰረት አድርጎ እንከን ለማይወጣለት የሆቴሉ ዘመናዊና ባህላዊ የአቀራረብ ውህደት የተሰጠ የእውቅና ደረጃ ነው፡፡

እጅግ ለላቀ የአገልግሎት አቅርቦቷ ኢሊሊ እስካሁን ከስምንት በላይ ሽልማቶችን ተቀዳጅታለች፡፡ እነዚህ ሁሉ የኢሊሊ ስኬቶች ያለ ውድ ደንበኞቿ ፣ የሥራ አጋሮች እና ያለ ራዕይና ተልዕኮዋ ማዕከል የሆኑት ባልደረቦቿ እውን አይሆኑም ነበር፡፡

## 13.5 Awards to the Hotel

The hotel was awarded "5 stars" by the Ethiopian Ministry of Culture and Tourism based on the Hotels star rating result by UN Tourism Organization. This is the highest accolade given to hotels in the country. The starts are awarded for outstanding facilities, services, Human Resource capability and all-rounded customers' experience, which offers a perfect balance between contemporary and traditional. So far, Elilly has also received more than eight recognition awards for outstanding services from its customers. This success could have not come to Elilly without the commitment of its esteemed customers, business partners, and associates who are the central pillars to keep Elilly vision and mission.



The Professionalism and Selfless service of Elilly Associate has generated trust and respect from many thousands of clients and customers around the globe. These includes many branches of USA-Arm forces, Above Award presentation by United States of America mission to AU Ambassador Dr. Reubene Breigety II to Elilly International Hotel illustrates once again Elilly leap in modern hospitality. Mr. Gadissa Bultosa was there at USA Embassy with Elilly Managing Director to receive distinguished of service.

## 13.6 የኢሊሊ የሰው ሃይል ኃብት

በሆቴል አስተዳደር እና የአሰራር መመሪያ መሰረት የኢሊሊ ኢንተርናሽናል ሆቴል አምስት የስራ ክፍሎች መንግሥት ያስቀመጣቸውን የአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ የሚያዘውን በሰራተኞች ምልመላ ፣ ጥቅም እና ዕድገት ዙሪያ መመሪያውን በትኩረት ይተገብራሉ፡፡

የሆቴሉን ራዕይ፣ ተልዕኮ እና እሴቶች ለመግለጽ እንዲሁም ለአስተዳደራዊ መመሪያነት እንዲያገለግል በማሰብ የአመራር ቦርዱ ባወጣው የአሥተዳደር ማኑዋል ላይ የተቀመጡትን አንቀጾች በጥብቅ በመከተል ተግባራዊ ያደርጋል፡፡ ከዚህ ባሻገር ክህሎት፣ ልምድ፣ ለሥራው የሚኖር ቁርጠኝነት እና ለሆቴሏ ለመሥራት አዎንታዊ አመለካከት የተሞላበት የራስ ተነሳሽነት ለሰው ኃይል ቅጥርና ስምሪት እንደ ብራንድ ይታያል፡፡

## 13.6 Elilly's Human Capital

As the practice of Hotel Operation and Management, Elilly International Hotel's Five Divisions have considered seriously and applied the rules and regulations of the government, that is, the proclamation of Employer and Employee as its Standard of Operation, SoP, in the processes of selecting, benefitting and developing its employees. The Hotel strictly follows all necessary articles and put into practice the procedures stipulated in the Administration Manual that has been approved by the Board of Trustee to promote Elilly International Hotel's vision, mission and values on one hand and to be used as Administrative Guide on the other hand.







*U.S. Marine Corps Performing Salute to Ball*




*Africa Logistics Forum 2015*

የኢሊሊ ስኬት፡- የኢሊሊ ኢንተርናሽናል ሆቴል የሰው ኃብት ክፍል ፍላጎትን መሠረት ባደረገ መልኩ በውስጥና በውጭ ሙያተኞች የሚሰጡ የሠራተኞች የአቅም ግንባታና ልማት ሥልጠናዎች ላይ በከፍተኛ ሁኔታ ይሰራል፡፡ እስካሁን ከ26 በላይ ሥልጠናዎች በውስጥ ሙያተኞች የተሰጡ ሲሆን የውጭ ሙያተኞችም እንዲሁ በተለያዩ ደረጃዎች ሥልጠና ሲሰጡ ቆይተዋል፡፡ እነዚህ ሥልጠናዎች በሥራ አመራር ፣ በአገልግሎት አሰጣጥ እና በመስተንግዶ ዙሪያ የሠራተኞቻችንን የአፈጻጸም ብቃት ላይ በላቀ ሁኔታ ውጤት አስገኝቷል፡፡ በሁሉም የሆቴሏ አገልግሎት ማቅረቢያ ቦታዎች ላይ የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ የሚደረገው ጥረት ይቀጥላል፡፡

## ኢሊሊ የላቀ የፈጠራ ጥበብና መስተንግዶ ታቀርባለች

የኢሊሊ ምግብና መጠጥ ክፍል ከፍ ያለ የመስተንግዶ ስሜት ለመፍጠር ይሰራል፡፡ ከምግብ ዝግጅት እንዲሁም ከመጠጥ አቅርቦት የተውጣጡት ባልደረቦቻችን ከአስተናባሪዎቻችን ጋር በመሆን እያንዳንዱን የኢሊሊ እንግዳ ግሩም ድንቅ ስሜት እንዲሰማው በማድረግ እውነተኛ ኢትዮጵያዊ መስተንግዶንና እንግዳ ተቀባይነትን እንዲያጣጥም ለማስቻል የቱንም ያህል ርቀት ይሔዳሉ፡፡

አዲስ አበባ የተባበሩት መንግሥታት፣ የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን፣ የተለያዩ የመንግሥታቱ ድርጅት ኤጀንሲዎች እና የአፍሪካ ህብረትን ጨምሮ የበርካታ ኤምባሲዎች እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች መቀመጫ ናት፡፡ ስለዚህም የስብሰባና የማስተናበሪያ ስፍራ የኢሊሊ ኢንተርናሽናል ሆቴል ሌላኛው ትልቁ የሥራ ክፍል ሆኖ ራሱን የቻለ አቅርቦት የተሟላ ቡድን የተመደበለት ሲሆን ማንኛውም ስብሰባ የሚጎድል ነገር ሳይኖረው በአግባቡ እንዲካሔድ ለማስቻል ዘወትር በአካባቢው ላይ የሚገኝ የተለየ ሥራ አስኪያጅ እንዲሁ ተመድቦለታል፡፡

በከተማዋ ካሉ ጎልተው ከሚታዩ ሌሎች ትላልቅ የሆቴል ብራንዶች በተለየ መልኩ ኢሊሊ ኢንተርናሽናል ሆቴል በራሱ ፈጠራ ፊትለፊት የሚያሰልፈው በልዩነት ተነጥሎ የሚታይበት ምስል አለው፡፡

የምግብና የመጠጥ ክፍላችን ለእያንዳንዱ ማዕድ የሚሆን የራሱ የሆነ መለያ በመፍጠር ሒደት ላይ ይገኛል፡፡ እያንዳንዱን የኢሊሊ ገበታ ቃና ፣ አበሳሰል እና የመጠጥ አመራረጥ ብሎም አጋጌጥ ለይቶ ለማወቅ ማንም አይቸገርም፡፡ ሆኖም የሚቀርበው መስተንግዶ እያንዳንዱ የኢሊሊ የምግብና የመጠጥ ባለሙያ እንኳን የሰለጠነበት ኢትዮጵያዊ የመስተንግዶ መልክ ነው፡፡

**“ችሎታ ከጠረጴዛ ጨው የቀለለ ነው፡ ፡ ችሎታ ያለውን ሰው ከስኬታማ ሰው የሚለየው ብዙ ከባድ ሥራ መሥራቱ ነው።”**

እስቴፈን ኪንግ

**“Talent is cheaper than table salt. What separates the talented individual from the successful one is a lot of hard work. ”**

Stephen King

Elilly Success: - Elilly International Hotel's Human Resource Division aggressively work on its employees capacity building/development by organizing need based trainings conducted by internal and/or external experts. There have been more than 26 trainings conducted mainly by internal experts; external trainers have been also conducted training at different capacities. These trainings greatly impacted our staffs' performance in management, service rendering and hospitality areas. The efforts are to be followed to bring more impact on our hotel service rendering at all areas.

## Elilly Displays Its Greatest InoovationTalent and Hospitality

Hospitality that feels like an upgrade-that's what Food and Beverage Division of Elilly International Hotel works on. Making each guest experience a WOW feeling, our Food and Beverage Associates and our Line Staff both from Food Production to Food and Beverage service walk that extra mile to make each individual guest feel the spirit of true Ethiopian Hospitality.

Addis hosts important United Nations Offices as well as the African Union Headquarters with numerous Embassies and NGO's. Therefore, for Elilly conferencing and conventions are a big division within itself. Elilly International Hotel offers numerous convention venues with having its own dedicated team for convention and banquets as we have specially designated approach Manager who is always available for any requirements that may be needed throughout full conventions held at Elilly International Hotel.

Unlike Bigger Hotel Brands visibly seen in Addis, Elilly International Hotel has its own individuality and image which sits at front row in innovation. We strongly believe in offering our guests genuine Ethiopian Hospitality with a touch of international standards, making our guests feel like home away from Home.

Our Food and Beverage Division is moving steadily on branding its own image for each of our dining outlets. One would not fail to notice that each dining outlet at Elilly International Hotel has its own flavor be it in cuisine, beverage selection or decor. But the Hospitality offered is the image of Ethiopian Hospitality which each Food and Beverage Associate of Elilly International Hotel is trained for.

At Elilly International Hotel, our core Managers believe in constant and relevant need-based training that is benefitting our line employees to attain

የምግብና የመጠጥ ዝግጅት ክፍሉ ከሌሎች የተለየና የራሱ የሆነ መልክ ፣ መለኪያና ስታይል በመፍጠር ብሎም በማስቀጠል በእጅጉ አምኖ እየሰራ ይገኛል፡፡ በዚህም መንፈስ ከዳይሬክተሩና ዋና ሼፉ አንስቶ እስከ አስተናባሪዎቹ ድረስ ሁሉም በአንድ ቡድን ይሰራሉ፡፡

በኢሊሊ ኢንተርናሽናል ሆቴል ያሉ ዋና ሥራ ኃላፊዎች ፍላጉትን መሰረት ባደረጉ ተከታታይ ሥልጠናዎች አስፈላጊነት የሚያምኑ ሲሆን ይህም እንግዶችን እጅ እየነሱ የሚቀበሉ አስተናባሪዎቻችን የላቀ ሙያዊ አቀራረብ እንዲኖራቸው ብሎም ክህሎታቸውን ለማሳደግ ለማስቻል ነው።

ከዚህም በኋላ እንግዶቻችን ወደ ሆቴላችን ከመጡበት ቅፅበት አንስቶ በምናቀርብላቸው ግሩም ድባቦች ልዩነቱን ያጣጥማሉ፡፡ እኛም እንዲህ እንላለን እንግዶቻችን በፈለጉት ጊዜ ወደ ሆቴላችን ጎራ ማለት ይችላሉ ወደ መጡበት በሚመለሱበት ወቅት ደግሞ የኢሊሊን መስተንግዶ በየራሳቸው ቀንጭበው ይዘው ይሔዳሉ፡፡

እኛ ኢሊሊዎች የተለያዩ የሆቴል አማራጮች እንዳለዎት ብናውቅም በሥራም ይሁን ለመዝናናት ተጓዥ ከሆኑ ፍላጎትዎን በላቀ ሁኔታ ለማሟላት ንጽህናቸው ከተጠበቁ እንከን አልባ ምቹ ክፍሎቻችን ጋር ፍጹም ትህትና በተላበሰ አገልግሎት ከተመጣጣኝ ዋጋ ጋር ልናስተናግድዎት ምንጊዜም ዝግጁ ነን፡፡

## 13.7 የኢሊሊ ሆቴል መገኛና አድራሻ ለአገልግሎት ትዕዛዝዎ

ኢሊሊ ከተባበሩት መንግሥታት የስብሰባ ማዕከል (UNCC) ትይዩ የከተማዋ እምብርት በሆነውና እየፈካች ባለችው ካዛንቺስ ትገኛለች፡፡ ከቦሌ ዓለም አቀፍ አይሮፕላን ማረፊያ 6.1 ኪሜ ብቻ ይርቃል፡፡ የአዲስ አበባን ከተማ ዙሪያ ገባ በሁሉም አቅጣጫ ማየት በሚያስችለው በሆቴሉ አናት ላይ ካለው ልዩ (VIP) ባር እና ሬስቶራንት የመናፈሻ እይታን ይጋብዛል፡፡ በተፈጥሮ አየር የታደለችው አዲስ አበባ የሙቀት መጠን በክረምት ዝቅ ሲል 10 ዲግሪ ሴሊሽየስ ይደርሳል በበጋ ደግሞ እስከ 28 ዲግሪ ሴሊሽየስ ከፍ ይላል፡፡

የኢሊሊን አገልግሎት ለማግኘት እባክዎ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት አድራሻዎች ይጠቀሙ፡፡

ካዛንቺስ የቢዝነስ ቀጠና
ቂርቆስ ክ/ከተማ 17/18
ስልክ: +25115587777 | +25115587778
ፋክስ: +25115585200
ፖ.ሣ.ቁ: 29118, Addis Ababa, Ethiopia
ኢ-ሜል: infor@elilly.com.et
ድረ-ገጽ: www.elilly.com.et

more professional approach towards our guest and upgrade their own skill set in Hospitality sector.

Moreover, the Food and Beverage operational division strongly believes and works towards creating and maintaining its own image, own standards, own style which is unique from the rest. Each of the Division's Associates works as a team, in this concept from the Director and the Executive Chef to the line servers.

In the future, our guests will feel the difference and experience the WOW touch that we offer from the time of check. We say one can check in anytime one's like but s/he takes a piece of Elilly Hospitality with her/him each time s/he goes away.

At Elilly International Hotel, whether you are traveling on business or pleasure, we know you have a variety of hotels to choose from. We strive to your choice... provide you a room that is clean and comfortable, with friendly attentive service at a value conscious price.

## 13.7 Elilly Location, Site Map, Contact and Reservations

Elilly is located at the very heart of the City next to United Nations Conference Center (UNCC). It is found in a locality called Kazanchis area where business is bubbling. Ride to the hotel only takes 6.1 km from Bole International Airport. The hotel offers breathtaking views from its rooms especially from the roof top Elilly VIP Bar & Restaurant where our customers almost take 360 degree view of the city, Addis Ababa. Addis Ababa is a naturally air conditioned City. The temperature ranges between a low of $10^{c}$ during the rainy season and a high of $28^{c}$ during the dry seasons.

Please contact the hotel directly if you would prefer to receive our service or make a reservation using the following details or via telephone or email.

Kazanchis Business District
Kirkos Sub-City 17/18
Tel: +25115587777/+25115587778
Fax: +25115585200
P.O. Box: 29118, Addis Ababa, Ethiopia
Email: infor@elilly.com.et
Website Address: www.elilly.com.et

# የኢሊሊ ኢንተርናሽናል ሆቴል ራዕይ፣ተልዕኮና እሴቶች
# Vision, Mission, and Values of Elilly International Hotel

## ራዕይ

ራዕያችን ለደንበኞቻችን የለቀ መስተንግዶ ማቅረብና ልዩ እርካታን መፍጠር ነው።

## ተልዕኮ

ለሁሉም ኢትዮጵያዊያንና ዓለም አቀፍ እንግዶቻችን ጥራቱን የጠበቀ ዘመናዊ መስተንግዶ በማቅረብ በባለ5 ኮከብ ሆቴል ደረጃ መስተንግዶ ልቆ መገኘት ነው። በሁሉም የመስተንግዶ መስኮች ተመራጭ ሆነን ለመገኘት የምንከተላቸው ስልቶች፡-

- ደንበኞቻችንን በላቀ ደረጃ ማርካት፣
- በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመታገዝ ለደንበኞቻችን እሴት መጨመር፣
- ለሠራተኞቻችን ጥራት ያለው ሥልጠና መስጠትና አመቺ የሥራ ሁኔታን መፍጠር፣
- ጠንካራና ራዕይ ያለው የማኔጅመንት ቡድን መፍጠር፣
- አዳዲስ ሃሳቦችን ማፍለቅና የኢሊሊ ልዩ ብራንድ የሆኑ አዳዲስ መስተንግዶዎችና አገልግሎቶች ማቅረብ፤

## እሴቶች

- በሁሉም አገልግሎታችንና ሥራዎቻችን መልካም ሥነምግባር መጠበቅ፣
- ለደንበኞቻችንና ተወዳዳሪዎቻችን ከፍተኛ አክብሮት መስጠት፣
- ለሁሉም ሠራተኞች ፍታዊ የቅጥርና ዕድገት ዕድል መስጠት፣
- አዳዲስ የመስተንግዶ ዘዴዎችን ያለማቋረጥ መፈለግና የአገሪቷ የሆቴል ኢንዱስትሪ እንዲያድግ አዳዲስ ሃሳቦችን ለሌሎች ማጋራት፣
- ለሆቴላችን ዕድገት በጋራ መሥራትና ኃላፊነትን መቀበል፣
- እንግዶቻችንን ለማርካት የኢሊሊን ጥራት ደረጃ በጠበቀ መልኩ የሚቻለውን ሁሉ ማድረግ፣
- የአካባቢያችንን ህብረተሰብ ማሳተፍና መልካም ግንኙነት መፍጠር።

## Elilly Vision

Our mission is simple; to provide authentic hospitality by making a difference in the lives of the people (customers) we touch every day.

## Elilly Mission

Our mission is to excel and lead in offering international standard five star services to our customers with emphasis on quality of modern hospitality to all Ethiopians and International community at large. We focus on this mission in pursuit of our goal of becoming the most preferred brand in each segment that we serve for our associates, guests, and owners through.

- Exceeding in all our customers' needs and expectations of our products and services
- Producing value added customer services supported by the state of the art technologies
- Providing quality training to associates and creating a good feeling Elilly work environment.
- Creating a forward looking and vibrant Elilly Management team.
- Striving constantly for new /innovative hospitality product/service ideas that are exclusive to the Elilly Brand.

## Elilly Values

We support our mission and goal by adhering to a set of deeply held core values that characterizes and drives Elilly Brand.

- Ethical behavior in all our service aspects and in our business practices
- Respect for all our diverse customers and high regard to our competitors success
- Equal opportunity for all men and women in terms of employment and ptersonal development
- Continuous quest for new modern hospitality concepts and sharing with others to help Ethiopian hospitality grow
- Collective responsibility through team work for Elilly success
- Doing everything for the benefit of the guest without compromising the quality of Elilly products/services
- Sound community relationship through community involvement and contribution.

GEBECON PLC

Etilly INTL Hotel
ADDIS ABABA
ETHIOPIA

# NOTE
# ማስታወሻ




Kazanchis Business District
Kirkos Sub-City 17/18
Tel: +25115587777/+25115587778
Fax: +25115585200
P.O. Box: 29118, Addis Ababa, Ethiopia
Email: info@elilly.com.et
Website Address: www.elilly.com.et

Elilly INTL Hotel
ADDIS ABABA
ETHIOPIA

*Your First Choice in Hospitality!*



Elilly INTL Hotel
ADDIS ABABA
ETHIOPIA

Elilly Multi Purpose Building Complex Design